# ምዕራፍ ስምንት

## የአቢሲኒያ ዕይታዎች፣ በተራሮች የታቀፈው የአሸንጌ ሀይቅ፣ የአልኮል መጠጣችን እንዲቀር መደረጉ

ከረዥም ጉዞ በኋላ እንደሚጠበቀው ሁሉ፣ ወታደሮች በሚቀጥለው ቀን መካን(መቃን) ላይ ማቆም ነበረባቸው፡፡

የአዲሱ ካምፓችን አካባቢው ብዙ ኗሪ ያለበት ነው፡፡ ተወላጆቹ እንግዶቹን ለማየት በብዛት ይመጡ ነበር፤ ሲመጡም የተለያዩ ነገሮች ለሽያጭ ይዘው ነበር፡፡ የዚህ አካባቢ ነዋሪዎች ከትግራይና ከአዲግራት ሰዎች ቀላ ይላሉ፡፡ እስካሁን ካየናቸው ሰዎች በሰውነት ፈርጠም ያሉና ሰፋ ያሉ ናቸው፡፡

በመሀከላቸውም ከኦሮሞ ምድር የመጡ፣ ራሳቸው ላይ ቱርባን ያደረጉ ሶስት ሙስሊሞች ረዘም ያለ ከበሬ ቀንድ የተሠራ ጥሩምባ እየነፉ ብቅ አሉ፡፡ ሰዎቹ፣ የኦሮሞው አለቃ መልከተኞች ናቸው፡፡ አለቃው፣ በህዝቡ ስም ለእንግሊዙ ንጉሥ፣ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ሰላምና ወዳጅነቱ ለማስታወቅ ነው፡፡ ምንም መግለፅ ባይኖርብኝም፣ ይህን የኦሮሞውን አለቃ መልካም ምኞት፣ ሽማግሌው በምስጋና ነው የተቀበለው፤ በአፀፋውም ቃል ለተገባው ወዳጅነት የገንዘብ ሽልማት እንዲሠጥ አደረገ፡፡

ሚዳቋዎች፣ ጥንቸሎችና ሌሎችም የሚታደኑ እንስሳት አንደልብ ነበሩ፡፡ የእንግሊዝ መኮንንኖችም እንደ ጀማሪ አዳኝ በገፍ ወጡ፤ በነባር ተፈጥሮ ላይ ያደረሱት ጉዳትም ከፍተኛ ነበር፡፡ ስሙ ያልተጠቀሰ አንድ ሰው፣ በአካባቢው የነበረ የጫካ ዝሆን ተኩሶ ገድሎ፣ ሽታው ሀገሩን ዙሪያውን እስኪበጠብጥ ድረስ ግዳዩን የወደቀበት ቦታ ላይ ጥሎት ሄዷል፡፡ አደኑ የተሳካላቸው ሁኔታ በስዕላዊ መንገድ የተነገረም አለ፤ እያንዳንዱም አንድ ወይም ሁለት ያደኑትን ይዘው ገብተዋል፡፡

በ18፣ በጥዋቱ ጦሩ ካምፑን ነቅሎ ወደ አሸንጌ ሀይቅ መንገድ ጀመረ፡፡

መሶብ ተራራ ግርጌ እስከንደርስ ድረስ፣ ለመጀመሪዎቹ ስድስት ማይሎች መንገዳችን ሸቅበና ቁልቁል ሆኖ፣ በግራና በቀኝ ከፍ ባሉ ኮረብታዎችና ጫካዎች የታጀበ ነበር፡፡ ተራራው ግርጌ ስንደርስ፣ ወደ ላይ እየታገልን ስንወጣ፣ እርስ በራሳቸው በሚደራረቡ ኮረብታዎች ተከበናል፡፡ ከዚህ በፊት በእግር ስጓዝ ያየሁትን የደቡባዊ ተራራማ ከፍል ይመስላል፤ ነገር ግን ይህ ትሮፒካል ውብት፣ በአቢሲኒያ ካየነው በፍፁም ተቃራኒ ነው፡፡ ሸቅበ፣

በረግረጉም አናናስ ዛፎች በተሸፈነ ቀጥ ባለ ዳገቶች ዙርያ በመውጣት ፍዳችን አየን፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ድንግል ጫካዎች ይታያሉ፤ በቀኝና በግራ ተስፋፍተው ወደ ላይ ማቆሚያ የለለው በሚመስል ከፍታ ተዘርግተዋል፤ በላያችን ላይ ደግሞ ደስ የሚል ቀዝቀዝ ያለ ጥላ ፈጥረዋል፡፡ በሚታየው ጥላቸው ስር ብርቅዬ የሆነ ቀለም ያላቸው አበቦች ፈንድቀዋል፡፡

ወደ ላይ ወደ ተራራው የሚወስደው መንገድ በጣም መጥፎ ነው፤ አንዳንድ ቦታም በጣም አደገኛ ነበር፡፡ ከአራት ማይሎች ቀጥ ያለ ዳገት በኋላ፣ ከዛፎቹ ጥላ ወጥተን፣ ሰማዩን ማየት ቻልን፤ ሌላ መጠነኛ ዳገት፣ መንፈስ በሚያረካ አረንጓዴ የተሸፈነ ቦታ ላይ ነው የቆምነው - እሱም የመሶብ ተራራ የመጨረሻው ከፍታ ነበር፡፡

ከታች፣ ከሰራችን፣ ከሶስት ሺ ጫማ በታች፣ የአሸንጌ ሀይቅ ዙሪያውን በከበቡት ተራራዎቹ ታፋ ላይ ያንቀላፋል፡፡

የጦር ሠራዊት አንድ ቦታ ቆሞ የአካባቢውን ውበት ለማየት ፍላጎቱም የለውም፤ ሁላችንም መሶብ ተራራ ላይ ቆመን፣ ለሰአታት ይህን ትሮፒካዊ ውበት ያለውን ዕይታ ብንመለከት ደስ ባሰን ነበር፤ ወታደሮቹ በብዛት እየተግተለተሉ በመምጣት ዙሪያችን ወረሩት፤ ወደፊት እንድንጓዝም ግፊት ነበረና መከላከል የማንችለው የተጓዦቹ ወታደሮቹ ማዕበል አብሮ ወሰደን፡፡

ከዚህ የተከተሉት ደግሞ፣ ከሸለቆው ስር ጠመዝማዛ መንገዶች፣ ወጣ ያሉ ቋጥኞች፣ አንድ ላይ አጅብ ብለው የሚገኙ አለቶችና ትልልቅ ድንጋዮች ነበሩ፡፡ አለቶቹና ድንጋዮቹ ብርቅ ባለው የፀሀይ ብርሃን ደመቅ ያሉ ቀለማት ያሳያሉ፤ አለዚያም በቋጥኙ ጥላ ወይም ወጣ ብለው በተንጣለሉት የዛፎች ቅርንጫፎች ጥላ ይሸፈናሉ፡፡

ዙሪያውን እየዞርን፣ መንገዳችንን በቋጥኝ ሸካራ የአለት ግድግዳዎች ጎን በማድረግ ወደላይ እየተጓዝን፤ ጥምዝምዝ ያለ ወራጅ ወንዝ የመሰለ መለመር ይዘን ራስ የሚያዞሩ ገደሎችን የሚያገናኙ መሻገሪያዎችን እየተጓዝን በመጨረሻ አሸንጌ ሜዳ ላይ ደረስን፡፡

ከአስራ አራት ማይሎች ጉዞ በኋላ፣ ከሀይቁ ጠጋ ብለን፣ ከፍት ያለ ቦታ ላይ ካምፕ አደረግን፡፡ የመንገዱ የተፈጥሮ ሁኔታ፣ ጓዝ የያዘውን ክፍል በጊዜ ከመድረስ ከልክሎታል፡፡ ፀጥና ረጋ ያለው የሀይቁ ውሀ፣ ከረዥም ጉዞ በኋላ የደከመውን ሰውነታችን ለማቀዝቀዝ ውስጡ እንድንነከር ገፋፍቶናል፡፡ ምንም አይነት ጉማሬ በቦታው የነበረ መሆኑን የሚገልፅ ምልከት የለም፡፡ ወይም ከሰው የባሰ ሌላ ከፉ አውሬ ለመኖሩም ምልከት የለም፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ከዚህ ቀደም፣ ከፉ አውሬዎች ያጋጥሟቸዋል ተብሎ ሲወራ የነበረውን ወሬ መሠረተ ቢስ ያደርገዋል፡፡



*በአሸንጌ ሀይቅ አጠገብ ጉዞ*

(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

በርግጥ ሁለት ወይም ሶስት የሆኑ በተክሎች የተሞሉ የተቋሩ ውሃዎች ከሀይቁ አጠገብ ነበሩ፡፡ እነሱም ቢሆን ከትንንሽ አሳዎች በስተቀር ሌላ አይነት ሕይወት አልነበራቸውም፡፡ ሀይቁ፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የተለያዩ የአእዋፍ ዘሮች አልፎ አልፎ ይታዩበታል፡፡ እነዚህም ዳክዬዎችን ጨምሮ የተለያዩ የባህር አሞራዎች ነበሩ፡፡

በኦሮሞዎች በኩል ባለው የሀይቁ ዳርቻ፣ ሰፋ ባለው ደን ውስጥ፣ ብዛት ያላቸው ሚዳቋዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነሱም ጋር፣ ተኩላ፣ ጅቦችና ግስላዎችም አሉበት፡፡ ነገር ግን ይህ ሥፍራ ደግሞ የሙስሊም አፍሪት* ያለበት ቦታ ነው፡፡ ተወላጆቹ በጣም በጭንቀት ተውጠው ሊነግሩን የፈለጉና እንዲገባን የጣሩበት ሁኔታ ነበር፤ ስለዚህ በዚህ ቦታ ማንም ፈረንጅ መሄድ የለበትም፤ ምክንያቱም አፍሪት ስላለ በማለት - ይቆረጣል፣(ጣቶቻቸውን ጉሮሯቸው ላይ የመቁረጥ ምልክት እያሳዩ፣ ምልክቱ ራሱ ይበቃል፡፡)

(*የሙስልማን አፍሪት ማለት ከፋርሰ አሀሪማን ወይም የስካንዲኒቪያን ሎከ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ያ ማለትም መጥፎ መንፈስ ወይም ጂኒ ማለት ነው)[109]

የሚያነቃቃ ዋናና ገላ መታጠብ ባይኖር ኖሮ፣ ምናልባትም ከነበረን ድካም የተነሳ መጥፎ መንፈስ መኖሩን ባልተከራከርንም ነበር፤ ነገር ግን፣ ጤናማ በሆነው ገላ መታጠብ ምክንያት ከነበረን ስንፍና ስለተነቃቃን የመጥፎ መንፈሱን ጉዳይ በጣም ነበር የተከራከረነው፤ እናም በተፍጥሯችን ባለን ሀሳብ ግትርነት፣ እንዲያውም በሀይቁ ዙሪያ እየጋለብን ሄድን፡፡ በኦሮሞዎች በኩል ያለው የሀይቁ ዳርቻ፣ ያለምንም ጥርጥር ምስጢራዊና የሰይጣን ወይም ቢታሪክ የሚጠቀስ ዲያብሎስ ቤት መኖሪያ በሚያስመስለው ሁኔታ በጣም አስፈሪና ፀጥ ያለ ነበር፤ በዚህም ምክንያትና በተጨማሪም በእእምሯችን ደግሞ ሰዎቹ ያሳዩን የእንገት መቁረጥ ምልክትም ስለነበር ወደ ውስጥ ገባ ብለን ቦታውን መመርመር ጥቅም የለውም ብለን አሰብን፡፡

ብዛት ያላቸው የበሰበሱ እንጨቶች በምስራቅ በኩል በሚገኘው በሀይቁ ዳርቻ አሉ፡፡ በሰሜን በኩል ያለው ዳርቻ፣ ከኛ ካምፕ በትንሽ ወደ ምስራቅ በኩል ወደ አምስት ማይሎች የሚሆን ስፋት ላይ ያለው ቦታ በጣም አደገኛ ነው፡፡ በጣም ሰፊ የሆነ የሚያዘቅጥ*፣ የረጋ ረግረግ ነው፡፡ ቦታው፣ ብዛት ባላቸው ልጋግ የመሰለ ነገር በተሞሉ ፈሳሾች እንደ ወንዝ መሰመሮች ይቆራረጣል፡፡ የመሬቱን አደገኛነት ከመገንዘቤ በፊት የኔ የአረብ ፈረስ እስከ ግማሹ ደረስ መስመጥ ጀመረ፤ ስለዚህ፣ ካምፕ ለመድረስ ሰፋ ባለ ከብ

---

109 በአንዳንድ የወንዝ ከፍሎቹ እንደዚህ ሠይጣን አለባቸው መባል የተለመደ ነበር፡፡

ዳርዳሩን መዞር ነበረብኝ፤ የሀይቁ ጠቅላላ ዙሪያው ወደ አስር ማይሎች ይሆናል።

(*በተወላጆቹ የሚነገር ታሪክ አለ፤ ይህም ሶስት መቶ የሚሆኑ የኦሮሞ ፈረሰኞች አቢሲኒያኖቹን ሲያሳድዱ በዚህ ቦታ ሲደርሱ አንድ ሰው ሳይተርፍ ሁሉም ወዲያውኑ በመስመጥ ተሰውረዋል።)

የመጨረሻው የጓዝ መስመሩ ከፍል ካምፕ ሲደርስ አኩለ ሌሊት ነበር፤ የኔ ጓዝ ወደኋላ ከነበሩት ውስጥ ስለነበር ድንኳኔ ከመወጠሩ በፊት ለአስር ሰአታት መጠበቅ ነበረብኝ።

የሚቀጥለው ቀን እንሰሶቹ መጓዝ ስላልቻሉ የግድ ማቆም ነበረብን። የነበረን ቀለብ እያለቀ ስለነበር፣ ከመንቀሳቀሳችን በፊት አዲስ ማግኘት ነበረብን። በዚህ ምክንያት የሚደርሰን መጠን በግማሽ ተቀነሰ።

አኩለ ሌሊት ሲሆን፣ ከትልቁ ገዥ መልከተኛ መጣ፤ ትልቁ ገዥ ወይም ኡሌማው፣ መንፈሳዊ መሪ፣ ንጉሥም ስለሆነ፣ በአሸንጌ ዙሪያ ባሉ መንደሮች ለሚኖሩ የሙስሊም ዘላኖች የሁሉም ነገር መሪ ነው። መልከተኛው ደግሞ የኡሌማው ወራሽ የሆነው ልጅየው ነበር። በሰውነት ቅርፅ መዳኝት የምችል ብሆን፣ መልከተኛው አይኑ የፈዘዘና አእምሮው ቢሆን የጥንቸል አይነት ነበር።

ለሰር ሮበርት ናፒየር የሚሠጥ ደብዳቤ ይዟል። በደብዳቤው፣ ባገሩ ባህል መሰረት ከሚደረገው ከተለመደው ሰላምታና መልካም ምኞት ቀጥሎ፣ ኡሌማው ከፈረንጆቹ ጋር ሰላም ለመፍጠር የሚፈልግ መሆኑን ይገልፃል። በመንፈሳዊ አመለካከቱም፣ አሪት፣ አዲስ ኪዳንና ቁራን፣ በኛ በክርስቲያኖቹና በሙስሊሞች ሀይማኖት መሀከል የጋራ መሆኑን ያሰረዳል፤ በፀሎቱም እንደሚያስታውሰን ነገረን፤ አላህ እንዲጠብቀን መረቀን፤ ጠላቶቻችን ብዙና ጠንካሮች ስለሆኑ እንድንጠነቀቅም መከረን። ባገሩ ደንብ መሠረትም ዋጋው አንድ ዶላር የሚሆን አንድ ማሰሮ ሙሉ ማር ላከልን።

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ የኦሮሞው መንፈሳዊ መሪ የላከውን ደብዳቤ ካነበበ በኋላ፣ በሰውየው ሥልጣን ደረጃ የሚሆን ሰው በመልበስ ሊያጌጥበት የሚችል የልብስ ስጦታ ለመልከተኛው ሠጠ። ይህንን አይነት በወርቅ የነቆጠ የሚያምር ልብስ ሲሰጠው፣ ሰውየው የተደሰተ መሆኑን የሚገልፁ የሰውነት ምልከቶች፣ ትንሽ ጡንቻ መንቀሳቀስ፣ ወይም አይን አርግብ ማለት፣ ወይም የፈገግታ ምልክት እንኳን ሳይታይበት፣ ስሜት የሌለው ከሰም የተሠራ አሻንጉሊት ይመስል ሳይነቃነቅ ቆሞ ቀረ።

ከሰአት በኋላ ደግሞ ሌላ የኦሮሞ አለቃ ከተዋጊዎቹ ጋር በመሆን፣ የወዳጅነት ምልክት እንዲሆን የጦሩ ጫፍ ወይም ስለታቸው የተቆረጠ የጦር ዘንጎች ይዘው ወደ ካምፕ መጡ። አለቃው በትክክል መልከኛ የሆነ ሰው

ነበር። ይህ የማርስ ልጅ የመሰለ ሰው ከኛ ንጉሰ ጋር ወዳጅነት እንደሚፈልግ ገለፀ፤ ስለዚህም ልክ ንጉሣዊ ሥልጣን ያለው ሰው የሚገባውን ከብር አይነት ተሠጠው።

ማምሻውን የተለየ ሁኔታ ታየ። ካምፕ በሚጠብቅ የሂንዱስታን ሰው፣ እንድ አሮሞ ለስርቆት ሲያመራ ስለታየ፣ ተይዞ በሌብነት ተከሶ ከጦር ወታደራዊ ዳኛ፣ ኮሎኔል ፍሬዝር ፊት ቀረበ። ወዲያውኑ ትልቅ ጉርምርምታ ይሰማ ጀመር። የሰውየው እገር ሰዎች ደግሞ፣ እንደ ጎሳ ባህላቸው ሰውየውን ለመጠበቅ በፍጥነት ከበቡና ለማስለቀቅ ሞከሩ። እንድ ወጣት፣ ወንድሙ ነው የተባለ፣ ከፍ ያለ ጩኸት አሰማ። ተጠርጣሪው እጆቹ ወደኋላ የፊጥኝ ታሰረው፣ ታምቡር ከተመታ በኋላ የወታደራዊ ፍርድ ችሎት ተያዘ። ኮሎኔል ፍሬዝር፣ ሰውየው በሰዎች እንደተያዘ ጀርባው ሰላሳ ስድስት ጊዜ እንዲገረፍ ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ካፒቴን ሰፒዲ ከነበረበት ግብዣ ተጣድፎ በመምጣት፣ ሰውየው በአገሩ ሰዎች ቢዳኝ ይሻላል ብሎ ሀሳብ እቀረበ። ፍሬዝር፣ በመቃወመ ለጦሩ ምሳሌ መሆን አለበት ብሎ ተከራከረ። ሰፒዲ ሊሚገት፣ ከአለቆቹ ጋር ሰላም ስለተፈጠረ፣ ከመጀሪያው በከባድ ቅጣት መጀመር ነገር መጫርና ደግነትም አለማሳየት ይሆናል አለ።

"ታዲያ ምን ማድረግ አለብኝ?" ፣ ፍሬዝር ጠየቀ።

"ያገሩ ሰዎች ይዳኙት፤ አንተ ከፈለግከው በላይ ከባድ ቅጣት ይሰጡታል።" አለ ሰፒዲ።

"መልካም፣ እንተ እንዳልከ ይሁን።" አለ ፍሬዝር። እንደተባለውም፣ የተጠርጣሪው ወገኖች ከሆኑ ሰዎች (ጁሪ) ዳኝነት የሚሰጡ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ሰዎቹ ያደረጓቸው ከርከርና ንግግሮች የኒውዮርክ ጠበቆች ሊከራከሩ ከሚችሉት በእሰር እጥፍ የሚሆን ተደጋግሞ ነበር። የሚገርም ነው፣ ያን የመሰሰ ሙግት፣ ያን የመሰለ ዘዴ፣ ያን የመሰለ ድርጊት!

ሸበቶ ጢም ያለው ሽማግሌ ያቀረበው ሙግት ፍሬ ነገሩ፣ ሰውየው ሊሰርቅ መፈለጉን ማንም መረጃ የለውም፤ በጁ ያነሳው ለማየት ብቻ ብሎ ነው። እና "ያ ወንጀል ነው ወይ?" ፣ ብሎ ጠየቀ። "ሆኖም፣" ቀጠለ፣ "መቅጣት ካለብን፣ ፈረንጁ እንዳለው፣ እሃ! እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ሀገር ሰዎች አይቀጡም፤ በነሱ ላይ እምነት መጣላችን ተሳስተናል። ስለዚህ፣ እኔ የምዳኘው፣ በዱላ ሰድሰት ጊዜ ተመትቶ፣ ሊሰርቅ ነው የተባለውን ዕቃ ዋጋ እንድ አራተኛውን ይከፈል።" በዚህ ፍርድ መሠረት ቅጣቱ ተከናወነ። አንዳንድ የወታደራዊ ሥነ ሥርአት አስጠባቂ የሆኑ ሰዎች ግን በሁኔታው ተበሳጭተዋል።

በ20፣ የእንግሊዝ ሠራዊት አንድ ሜዳ ያዘ፡፡ ሜዳው ከአሸንጌ ሀይቅ ዙሪያ ከሚገኘው ዝቅተኛ ቦታ ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ ከሀይቁ ሰሜን በኩል ከሚገኘው ከኛ ካምፕ ወደ ሰባት ማይሎች ርቀት መስጊታ ከተባለ ቦታ አጠገብ ነበር፡፡ ወደዚህ ካምፕ መሄጃው በሀይቁ በምዕራብ በኩል ነበር፤ ከካምፑ በደቡብ አቅጣጫ አራት ማይሎች ርቀት መስጊታ ይገኛል፡፡

የእንግሊዝ ጦር ከመስጊታ ተነስቶ አስራ አንድ ማይሎች በመጓዝ ወደ ላት ሄደ፡፡

እንዲያው የሚያደክም ድግግሞሽ ላለማድረግ፣ የዚህ መንገድ ጠባይ፣ ከዚህ ቀደም ካለፍንባቸው የብዙ ኮረብታዎች መንገድ ጋር ይመሳሰላል፡፡

ቢጋማ ከብት ላይ ለሚጓዙ፣ መንገዱ በጣም መጥፎ አልነበረም፡፡ ነገር ግን፣ በጀርባቸው ሃምሳና ወይም ስልሳ ፓውንድ ተሸክመው ለሚሄዱ እግረኞች ግን መግለፅ የማይቻል ስቃይ ነበር፡፡ እንዲህ አይነቱን ነገር ማሰብ ይመች እንደሆን እንጂ በተግባር መግለጡ የሚሆን አይደለም፡፡ ሙቀቱ ሀይለኛ ነበር፤ ማለትም በአማካይ፣ የሙቀቱ መጠን 98° ፋራናይት ነበር፡፡ ከዙላ ወደ ላት፣ በቀን የሙቀቱ መጠን ከ84° በታች ሆኖ አያውቅም፡፡ በማታ ሲሆን ግን የሙቀቱ መጠን ወርዶ ከ 30° እስከ 40° ፋራናይት ይደርሳል፡፡

ለስድስትና አራት ሰአት ጉልበታቸውን ጨርሰው ዳገቱን ከወጡ በኋላ ተራራው አናት ላይ ለተወሰነ ጊዜ እንዲያርፉ ተፈቀደላቸው፣ የደጋውን ንፁህ አየር ሲተነፍሱ፣ ለፈረሰኞችና እግረኞች የተትረፈረፈ ካሳ ማለት ነበር፣ ፡፡

እዚህ ያልተደላደለ ቦታ ላይ ድንኳናችን ወጥረን፣ ከብዙ ድካም በኋላ ራሳችን ለማዝናናት በምንዘጋጅበት ሰአት እፍታም ሳይቆይ ለተረጋጋው መንፈሳችን ሴላ ቅጣት ነው የወረደው፡፡ እሱም፣ የጀኔራሉ ረዳት፣ ኮሎኔል ተሲገር የሚያስፈራ ትዛዝ ስለሰጠ ነበር፡፡ ያመጣናቸውን መጠጦች ጥለን መሄድ እንዳለብን በሚመለከት፣ ዋናው እዛዥ ጓዙንና ድንኳኑን እዚሁ ላት ጥሎ ለመሄድ ስለወሰነ፣ የመጣው ትዛዝ፣ 20 ወታደሮች አንድ ድንኳን እንዲጋሩ፣ አስረ ሁለት መኮንኖች ደግሞ አንድ ላይ እንዲሆኑ ያስገድዳል፡፡

ይህ ትዛዝ በአንጣሎ ከተሠጠው ትዛዝ ሁለተኛው ክፍል ነበር፤ ያሁነኛው ግን በጣም ጠበቅ ያለና ድንገተኛም ነው፡፡ የመጀመሪያው ትዛዝ በህንድና-የእንግሊዝ መኮንኖች ሙሉ በሙሉ እንዳልተፈፀም ሰር ሮበርት ናፒየር ተገንዝበ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ፣ ምንም አይነት የጓዝ ሻንጣ ወደ ጦር ግንባሩ እንዲሄድ አልተፈቀደም፡፡ ሁሉም በቅሎዎች የስንቅና ትጥቅ ጓዞችን እንዲያጓጉዙ ተፈልገዋል፤ ፈረሰ ጫንቃ ላይ ያልሆኑ መኮንኖች እንዲይዙ የተፈቀደላቸው ካፖርት፣ ብርድልብስና ከላስቲክ የተሠራ ምንጣፍ ነገር ነው፡፡

የዕዞ ፅህፈት ቤት መኮንኖችና የፈረሰኛው ኤታ ማጆሮች፣ በፈረሶቻቸው የፈቀዱትን መያዝ ይችላሉ፤ ነገር ግን ሰር ሮበርት ናፒየር የሰጠው ሃሳብ፣ "ፍጥነት የሚያስፈልገው ግዳጅ ከመጣ ግን ፈረሶቻችን ደከሙ ብለው ለሱ አቤቱታ ማቅረብ አይችሉም።።"

በዚህ ከተሰማሙ ድንኳኖቻቸውንና የጓዝ ሻንጣዎቻቸውን መውሰድ ይችላሉ። ስኳር፣ ራም፣ ቡና፣ ሻይ፣ ድንች፣ ሽንኩርት የመሳሰሉት የቅንጦች ነገሮች ደግሞ ወደ ኋላ መቅረት አለባቸው፤ ምክንያቱም፣ መቅደላ ላይ ፈጣን እንቅስቃሴ ሊደረግ ስለታሰበ ነበር።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት፣ በመጠኑ ቀለል ካለ የጓዝ መሰመር ጋርና ቁጥራቸው ያነሰ ድንኳኖችና የጓዝ ሻንጣዎች ጋር፣ ካምፑን በትነን ወደ ማርዋ መንገድ ጀመርን። እንደ ኮሎኔል ፋይሬ ስሌት አሰር ማይሎች ይርቃል፤ ኮሎኔሉ፣ ርቀቱን ለከቼዋለሁ ነው የሚለው።

በአንጣሎ የተሠጠው ትዛዝ የመኮንኖችን ስሜት ለመገመት ሊባል ቁርጥ የሆነ አልነበርም። የአሁኑ የመጨረሻው ግን የማያወላውል፣ ጠበቅ ያለና የማይቀር ነበር። ስለዚህ ቅሬታና፣ ውስጥ ለውሰጥም ቢሆን ጠብ የመፈጠር ሁኔታ በወታደሮች ታይቷል፤ ወታደሮች ጨመር ባለ ሁኔታ ማጉረምረም ጀምረዋል፤ በጊዜ ካልተያዘ ደግሞ ወደ አመፅ የሚያመራ ነበር።

ወደፊት የሚመጡት ረዥም ጉዞዎች ደግሞ ነገሩን ያባባሱት ይመስላል። ሰዎች መናገር ጀመሩ፤ ይህንን ደግሞ ወደ ጠቅላይ ዕዙ የሚያቀብሉ ሌሎች ሰዎች ነበሩ። ሲያጉረመርሙ ምንም አይነት መልስ ስላልተሠጠ፣ ወታደሮቹ ከየመኮንኖቻቸው ፊት ያለምንም ፍርሃት መናገር ጀመሩ፤ የሰር ሮበርት ናፒየር ረዳቶች ፊትም ቢሆን። ኮሎኔል መክሊአድ፣ የአዛዡ ረዳት ጄኔራል፣ በወታደሮች አጠገብ ሲያልፍ ልክ መንፈስ እንዳለፈ አይነት፣ ያሰተዋለው ወይም ያወቀውም ሰው አልነበረም። በጣም ተናደደና፣ ለመኮንኖች ያላቸው ክብር የት ሄደ በማለት አጥብቆ ጠየቀ። እነዚህን ውነታዎችን ለሰር ሮበርት ናፒየር ሪፖርት አደረገ።

ያን ቀን ማታ፣ አስራ ሶስት ማይሎች ከተጓዝን በኋላ ማርዋ ላይ እቆምን። በሚቀጥለው ጥዋት ወደ ዲልዲ መንገድ ጀመርን። ተራራዎች ከፍና ከፍ እያሉ፣ አካባቢው ደግሞ ሰው አልባ እየሆነ ነበር። ወዴትና በምንስ መንገድ ነው የዚህ ጉዞ ማብቂያው?

ቴዎድሮስ እነዚህን ሰው ሊወጣቸው የማይችሉ ኮረብታዎችን አልፈው ከሄዱ፣ መቅደላ ምን ሊመስል ይችላል? አሁንም ቢሆን ወታደሮቹ እያጉረመረሙ ነበር፤ በተለይ የ33ኛው ወታደሮች የሚያደርጉት ጉልህ ነበር። ኮሎኔል ፋይሬ የዚህን ጉዞ ርቀት አሰር ማይል ብቻ ነው ብሎ ነበር። ነገር ግን

ከአስራ ስምንት ማይል በላይ ሆኖ ነው የተገኘው፡፡ ወታደሮች፣ ከብት ጫኞቹና እንስሶች በቁጥር በደርዘን መውደቅ ጀመሩ፤ እንዲያውም በሃምሳዎች የሚቆጠሩም፣ ይህ ሁሉ ከፍፁም ድካም የተነሳ ነበር፡፡

ወደ ጉዞው ማለቂያ አካባቢ ሰዕላዊ የሆኑ ሸለቆዎችን ማየት ጀመርን፤ በሁሉም በውስጣቸው ወራጅ ውሀዎች ይታያሉ፡፡ የደከሙት ሰዎች በወራጅ ውሀዎቹ ዳርቻ ማረፍ ጀመሩ፤ ካምፕ ለመስራት ተስፋ የቆረጠ በሚመስል ሁኔታ ነበሩ፡፡

ከምሽቱ አስራ አንድ ሰአት ሲሆን፣ የተወሰነ የጦሩ ክፍል ብቻ ነበር ካምፕ የደረሰው፡፡ በድካም፣ በየቡድኑ ሆነው ሲመጡ፣ ከኮረብታዎቹ ጀርባ አንድ ሺ የሚሆኑ ሰዎች ገስግሰው ቢደርሱባቸው የነበረውን ሀይል በሙሉ መደምሰስ ይችሉ ነበር፡፡ በመጨረሻ፣ ወታደሮቹ ከአዲሱ ቦታቸው ዲልዲ ሲደርሱ እኩለ ሌሊት ነበር፡፡ የጓዝ መስመሩ በረሃብና በጉዞ ደከሞ በነጋታው ጥዋት አራት ሰአት ድረስ አልደረሰም ነበር፡፡

በዚህ በተቆራረጠ ጉዞ ምክንያት ዲልዲ ላይ አንድ ሙሉ ቀን መቆየት ነበረብን፤ አሳዛኝ ሆኖ ጦሩም ይህ እረፍት ያስፈልገው ነበር፡፡

ጠዋቱን፣ የ33ኛው ሬጅመንት አግረኞች ማስጠንቀቂያ በሰጣቸው በሰር ሮበርት ናፒየር ፊት ተጠሩ፤ ባሳዩት ባህሪም፣ ለአበሲኒያ ዘማች ጦር አሳፋሪዎች ናችሁ አላቸው፤ በመጨረሻው ጉዞ ላይ ሰላደረጉት ማጉረምርም ከመኮንኖች የሰማ መሆኑን ገልፆ፣ በዚህ በማይመስል መንገድ ፀባይ ለማሳየት ደስተኛ ሰለነበሩ ቀዳሚ ጦር የመሆን ከብሩን አይሰጣቸውም፤ ሰለዚህ ዝቅ በማድረግ፣ በሰር ቻርለስ ስታቨሊ ስር ሆነው የኋላ ደጀን ይሆናሉ፡፡ በነሱ ምትክ 4ኛው (የንጉሡ) የነሱን ቦታ ይወስዳል፡፡ በፀጥታ፣ ያለምንም እንቅስቃሴ ቆመው፣ በተከፋ ልብና ሀዘን፣ የአዛዣቸውን ማስጠንቀቂያ ሲሰሙ ያየ ማንም ሰው ያዝንላቸው ነበር፡፡

የ33ኛው ሬጅመንት፣ በብሪትሽ ጦር በጣም ጥሩ የሚባሉ ሰዎች ያሉበት ነው፤ እንደዚህ በቅፅበት ሲዋረዱ መታየት፣ ለነበራቸው ዝና ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡ ከዚህ በፊት፣ የዚህ ክፍል የነበረው (የዌሊንግተኑ መስፍን) የሚባለው ጦርም በሠርጥ አካባቢ ባሰየው የግድየለሽነት ባህሪ ይኸው ሬጅመንት ተቀጥቶ ነበር፡፡

የዲልዲ ካምፕ በጣም የሚያምር ገፅታ ያለው ቦታ ነበር፡፡ ጠበብ ያለ ሸለቆ ሆኖ በደን በተሸፈኑ ኮረብታዎች የተከበበ ነበር፤ በውስጡም ማያ የተባለ ትንሽ ወንዝ ይወርዳል፡፡ ከትናንትናው ድካም በኋላ፣ ይህ ትንሽ ወንዝ ለኛ ኤደን ማለት ነበር፡፡ ሁላችንም፣ በነፃነት፣ በልጅነታችን ስናደርገው እንደሚያስደስትን ወንዙ ውስጥ ተነከርን፡፡ በአቢሲኒያ፣ የውነተኛ ወንዝ ስናይ

የመጀመሪያው ነበር፤ ቀስ በቀስ ስለወንዙ ባለቅኔ መሆን ጀመርን:: ወንዙን የተለየ ስሜት የሚሰጠው ሌላ ባህሪ ነበረው:: ወንዙ ከጊዜ ብዛት መሬቱን ቦርቦሮ ጥልቀት ስለነበረው፣ በጎንና በጎን ያሉት ዳርቻዎቹ፣ ከሃምሳ እስከ ሁለት መቶ ጫማዎች የሚሆን ቀጥ ያለ ከፍታ አላቸው:: እነዚህ የወንዙ ዳርቻዎች ደግሞ ብርቅየ በሆኑ ተክሎች የተሸፈኑ ነበሩ::

የቃኝዎች ጦር አዛዥ የነበረው ጄኔራል ፊልድ የኛን ወደ ዲልዲ መምጣት ለሁለት ቀናት ሲጠብቅ ነበር:: እኛ ካምፑ የደረስን እለት፣ ከስንቅና ትጥቅ ክፍሉ ከኮሎኔል ፋይሪ ጋር በመሆን ወደሚቀጥሰው ማረፊያ ቦታ አመሩ:: ቦታው ወንዳጅ ይባላል፤ በዚያም፣ ከነኛው ብርጌድ የአንድ ቀን መንገድ ቀድሞ ለመሄድ ነበር::

በሚቀጥለው ቀን፣ ጦሩ፣ መዝገር አምባ በሚባል ተራራ ዳገት ላይ ጉዞውን ቀጠለ:: አቀበቱ በማያቋርጥ ሁኔታ የከፍታው ማቆሚያ የለውም ብለን እስከናምን ድረስ፣ በዳገታማ ኮረብታዎች ወደ ላይ ይወጣል::

እኩለ ቀን ሲሆን፣ ከባህር ወለል በላይ የ10,700 ጫማዎች ከፍታ ያለው የመዝገር አምባ እናት ላይ ወጣን:: በዚህ ከፍታ ላይ የአየር ፀባዩ ከበጋ ሙቀት ወደ አርክቲክ በታች ወደሆነ ቅዝቃዜ ሲለወጥ ተሰማን:: ያጋጠመን፣ ቀዝቃዛ በረዶ ያለው ካፊያ፣ ዝናብና እንደበረዶ የሚቀዘቅዝ ወጀብ፣ የበጋ ልብሳችን እንደለበሰን እንድንቀጠቀጥ አደረገን::

ችግር ጓደኝነትን ይወዳል ይባላል:: የተሰማንን ችግር ለመጋራት ድንኳናችን ትተን፣ በዚህ ቀዝቀዛ ጭቃማ ቦታ የተረገመ ሁኔታ የሚፈጥረውን እርስ በርስ ወሬ ጀመርን:: ዲልዲ ሸለቆ እያለን፣ አርቀው ማሰብ የሚችሉ ብልሆች ለማገዶ የሚሆን እንጨት በድንኳናቸው ውስጥ አስቀምጠው ነበር:: እነሱ ባቀጣጠሉት እሳት ዙርያ ሙቀት ለማግኘት እንግዶች ይመጡ ጀመር፤ እንግዶቹም በዚህ እሳት ዙሪያ ቆመው ልባቸውን በመክፈት የእሳቱን ባለቤቶች ያደንቁ ነበር::

የኮረብታው ዳገቶች ምንም አይነት የእንጨት ምልክትም የለባቸውም:: የነበሩት ተክሎች፣ እንጨት መምሰል የሚቃጣቸው ቢኖሩ፣ ብዛት ያላቸው የዝንባባ ዛፍ ቅጠል የሚመስል ያላቸው ተክሎች ነበሩ:: እነሱም ቢሆን ለማገዶነት አገልግሎት የሚውሉም አልነበሩም:: እነሱን እንደ እንጨት ለማንደድ ከተፈለገ መጀመሪያ በእሳት መጠበስ ወይም መሞቅ ነበረባቸው:: ያገሩ ተወላጆች ለኮሚሳሪያቱ የማገዶ እንጨት እንዲያቀርቡ ተጠየቁ፤ ከፀሀይ ግባት ከአንድ ሰአት በኋላ፣ የልጃገረዶች ቡድን፣ በጭንቅላታቸው የእንጨት ጭነቶች ተሸክመው ካምፕ ድረስ መጡ፤ ይህም ካምፑ ውስጥ ያሉ ሰዎችን

በሙሉ ከልባቸው እንዲደሰቱ አደረጋቸው። መሸት ብሎ ማታውኑ፣ የ4ኛው(የንጉሡ)፣ 33ኛውን ለመተካት ካምፕ ደረሱ።

አራት ሰአት ሲሆን፣ ጦሩ ካምፑን አፍርሶ የመሾገር አምባን ቁልቁለት በመከተል ስድስት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ ሙጃ ተጓዘ። መንገዱ በአንድ ቁልቁለት ላይ በመውረድ እያዘገመ ወደ ተከዜ ይወስዳል። በመንገዱ በግራ በኩል የተከዜ ወንዝ ይወርዳል፤ ከመነሻው ትንሽ ወራጅ ውሃ ነው፤ ነገር ግን በምዕራብ በኩል ከአንድ መቶ ማይሎች በኋላ ትልቅ ወንዝ ይሆናል።

የሙጃ ካምፕ፣ በተከዜና በአንድ ትልቅ የገደል ዳርቻ ያለው ሸለቆ መሀከል ነው፤ ገደሉ በቂ የሆነ ውሃ እንዳናገኝ አድርጎናል።

በሚቀጥለው ጠዋት፣ ከሙጃ ተነስተን ወደ ሳንታሪ ተጓዝን፤ ስሙ የመጣው ዋድላ አምባ ላይ ከሚገኝ ሳር የበዛበት ጉብታ ላይ ካለ መንደር ነው።

ከሙጃ ተነስተን የተጓዝን ቀን፣ በአቢሲኒያ ብሩህ ከሆኑ የፀደይ ቀኖች አንዱ ነበር። ለመጀመሪያዎቹ ሰባት ማይሎች መንገዱ ወደ ተከዜ በሚያወርደው በመሾገር አምባ ቁልቀለት ላይ ነበር። በጣም በዝግታ የሚወርድ ቁልቁለት ነው የነበረው፤ ምክንያቱም ዳገትነቱ የአስራ አራት ማይሎች ርቀት ነበረው። መንገዱ በግራና በቀኝ መስመሮች ማለትም ሸለቆዎች መሀል ነው፤ አንዱ በግራ ሲወርድ፣ ሌላው፣ ተከዜ በመሀሉ የሚወርድበት በቀኛችን በኩል ነበር። ከመሾገር አምባ ተነስቶ አስራ አራት ማይሎች ወይም ከሙጃ ተነስቶ ሰባት ማይሎች ከተጓዝን በኋላ፣ ተከዜ፣ በድፍረት በድንገት ይታጠፋል።

ተከዜ ስንደርስ፣ ወደ መጣንበት ወደኋላ ካልተመለስን በስተቀር ወይም የሌላውን ሸለቆ ጠመዝማዛ መንገድ ይዘን ካልሄድን በስተቀር በተከዜ ታጥረናል።

"ወደኋላም ተመልሰን አንሄድም፤ ሸለቆውንም ተከትለን አንሄድም።" ካፒቴን ስፒዲ ነበር የተናገረው፤ "ነገር ግን፣ ከፊት ለፊት የምታዩትን ማቆሚያ የመሰለውን ግድግዳ መውጣት አለብን።"

"ታላቁ ቄሳር!"

እንደውነቱ ከሆነ፣ ወደ ላይ ሰማይ ያቀፍ የሚመስል ያንን የአለት ግድግዳ ሲያዩ፣ አብዛኞቹ ሰዎች ይህንን ቃል በተናገሩ ነበር። ነገር ግን፣ በናፒየርና በሚከተሉት ሰዎች፣ ሁለት ቀናት የሚወስድ ቢሆንም እንኳን፣ መደረግ የሚገባው ነገር ይደረጋል።



የአርምስትሮንግ ከባድ መሳሪያዎች በተከዜ ሸለቆ ሲጓጓዙ
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

የብረት መንፈስ ያላቸው የ4ኛው ወታደሮች ቀጥ ባለው ግድግዳ ላይ ግማሹ ላይ ደርሰዋል። ግራና ቀኝ፣ ወዲያና ወዲህ፣ ዚግዛግ በሆነ መንገድ እርስ በርስ እየተሰባጠሩ፣ ዙረያውን በዳገቱ እየተጠማዘዙ ወደላይ ይወጣሉ። ሌሎቹ ሠራተኞችም መንገዱን ለመሞከር ቆርጠዋል፤ ፈረሶቻችን ኮልኩለን ወደላይ ዳገቱ ላይ መግፋት ጀመርን። ከግማሽ ሰአት በኋላ አንደኛውን እርከን ወጣን። ቀስ እያለ ከፍ የሚል ዳገት ፊት ለፊታችን ነበር፤ ከሶስት ወይም አራት መቶ ያርዶች በኋላ ሌላ ተመሳሳይ ከፍታ ያለው እርከን ላይ መወጣት ነበረበት፤ ይህንን እንዳሳካን፣ ትንፋሽ ለመያዝ ቆም አልን፤ በዚያም የሚያስገርመውን ተፈጥሮ ገፅታ ለማየትም ነበር።

ወደላይ በወጣን ቁጥር የተፈጥሮ ዕይታ ግርማ እየጨመረ ነበር የሚሄደው። በሚያምር የፀሀይ ብርሃን ስር፣ ኢጣልያ ጉራ የምትነፋበት የሚመስል ለማያዊ ሰማይ ስር፣ ድንግል የሆነው መሬት ተንጣሎ ይታያል። ወደ መቅደላ መንገዳችን በቀጠልን ቁጥር፣ በየቀኑ፣ የቦታው ወጣ ገባነቱ እየጨመረ ነው የሚሄደው። የተራራዎቹ አናቶች ብርቅ ባሉ በፀሀይ ጮራዎች ተውበዋል።

ወደላይ፣ ያለማቋረጥ እየደከምን ነው፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ለማረፍ እያቆምን ነበር። ፈጣንና ጠንካሮቹ የአረብ ፈረሶችም ቢሆን፣ በትንፋሻቸው እያቃተቱ ነበር፤ ጠንካራ የብረት ሰውነታቸው የተወጠረውን ነርቫቸውን የሚያፍታታው ይመስላል። ጠንካራ ዝርያ ያላቸው ቢሆኑም ተሸንፈዋል፤ እናም ባዶ ጉልበት ነው የቀረው፤ ሆኖም ረዘም ያለ እረፍት እንዲያገግሙ ያደርጋቸዋል።

እያንዳንዱ ከፍታ ማዕዘን ወይም የሚታጠፍ መንገድ ደንበኛ የሆነ መከላከያ ፈጥሯል። ላመል ያክል አንኳን የሚደረግ ጥረት የቶን ያህል የሚከብድን እለት ማንከባለል ይችላል። ከመጠን በላይ የሆኑ ትልልቅ ድንጋዮች ባሉበት ዳገት፣ አስር ጠንካራ ልብ ያላቸው ሰዎች፣ አንድ ሺ የሚሆነውን ሰው መመከት ይችሉ ነበር፤ እናም፣ በታሪክ ሌላ የቴርሞፓይሊ[110] ዝና በጨመሩ ነበር።

የእንግሊዝ ሠራዊት ተጠቃሚ ይሆናል፤ ማለቂያቸው ጥሩ የሆኑ ሁሉም ነገሮች ሂደታቸውም ጥሩ መሆን አለበት። "ፈጣሪ ከኛ ጋር"፣ የሚለውን የናፒየርን መንፈሳዊ ንግግር በማስተጋባት፣ ወደላይ ከፍ እያልን እንወጣለን፤ እናም ከላይ ያለውን የአለም ከፍል እንደገናም እናያለን። ከውቅያኖስ በላይ

110 ቴርሞፓይሊ በሚባል ማለፊያ፣ ቁጥራቸው እነስ ባሉ ግሪኮችና የላቀ ቁጥር በነበራቸው ፋርሶች መካከል የተደረገ ጦርነት ነው። በሲኒማ፣ '300' በሚል ርዕስ ለህዝብ ቀርቧል።

የሚፈልጉትን ያህል በብዛት ገዙ፤ ለአንድ ሙሉ ቀን የሚሆን ነዳጅ አንድ ሙሉ ዶላር ነበር የሚያወጣው፡፡ ቀለብ በፍጥነት እያነሰ ነበር፡፡ እንስሶቻችን ከሚገባቸው ቀለብ በግማሹ አብዛኛውን ጊዜም እሩቡን ያህል ነበር የሚታደላቸው፡፡

እንስሶቻቸውን፣ መልሶ መሸጥ በሚቻልበት ጥሩ ሁኔታ መጠበቅ የፈለጉ ሰዎች፣ ከኗሪዎቹ፣ ማግኘት የሚችሉትን ያህል እህል መግዛት ነበረባቸው፡፡ ከለንቅ ከፍሉ በተጨማሪ እንደገና የአንድ ዶላር የሚሆን ዳቦ የሚያስፈልጋቸው ሠራተኞችም አሉ፡፡ ትንሽ ማር ወይም ወተት ሌላ ዶላር ያወጣል፤ ስለዚህ ባጠቃላይ አንጣሎን ለቀን ከመጣን ወዲህ፣ የኮሚሳሪያቱን ወጭ ጨምሮ የአንድ ቀን ወጭ ሰባት ዶላር ድረስ ይደርሳል፡፡ ሁለት መቶ ዶላር የያዘ ከረጢት ብዙ የሚቆይ ቢመስልም በአጭር ጊዜ ያልቃል፡፡

የዋድላ አፋፍ ብዙ መከራ እይቷል፡፡ ብዙ ጌዜ፣ ቴዎድሮስ ራሳቸው ጉልበታቸው ደከም ባለ ጊዜ ወረውታል፡፡ አሁን ደግሞ የዋግሹም ጎበዜና፣ የዋግ ሹሙ እጎትና የጦሩ አዛዥ የደጃዝማች መሸሻ ግዛት ነው፡፡ እኛ የደረስን ቀን፣ 1500 ወታደሮች ይዞ በላስታና በሰሜኑ ገዥ(መሰፍን) በዋግሹሙ የተጣለበትን ከባድ ግብር አልከፍልም ያለ አመፀኛ መንደር ለመቅጣት እይተንቀሳቀሰ ነበር፡፡

እኛ ሳንታሪ ሰንደርስ፣ ደጃዝማች መሸሻ በምስራቅ በኩል በሚገኘው መንደር ደርሶ ነበር፤ ወዲያውኑ፣ በሁለቱ የጦር መሪዎች መካከል የወዳጅነት መልከቶች ልውውጥ ተደረገ፡፡

ጠፍቷል ተብሎ ጭምጭምታ የተወራበት መንሲንጀር፣ በዚህ ግዛት እየኖረ፣ የሀበሻ እንጀራ እየበላ፣ በሰላም፣ በወዳጅ ካምፕ ሆኖ የደጃዝማች መሸሻን ጠጅ እየቀመቀመ ነበር፡፡ የፈረንሳዩ ቆንስላ፣ የሰላማዊ ዲፕሎማሲ ሥራውን በሚገባ እየሠራ ነበር፤ የጠርጣራውን የሀበሻ ጄኔራል ልብ ማሸነፍ ችሏል፡፡ እናም በጄኔራሉ ናፒየር ጥሪ መሠረት፣ መሸሻ፣ በነጋታው ወደ ካምፕ ለመምጣት ቃል ገብቷል፡፡

በደረቆቹ ኮረብታዎች በታቀፈው ካምፕ፣ በማያስጋ ቦታ ነው ያለነው፤ ሲመዘዝን፣ በግማሽ ራሽን እንደሚጠበቀው ከሚሰቃዩ ሰዎች የተሻለ ነበር፡፡ ሆኖም መጠጥ አልነበረም፤ ዳቦውም መጥፎ ነበረ፡፡ የዋድላ ተራራ በጣም ይበርዳል፤ ከታች ከሸለቆው የምጣድ ያክል ካለው ሙቀት ጋር ሲወዳደር፣ እንደ ሪፍሪጂሬተር ማለት ነው፡፡ በመጣን በጠዋቱ፣ የተገኘው ከፍ ያለ ቦታና ዳገቱ በሙሉ በረዷማ በሆነ ጤዛ ተሸፍኗል፡፡ የነበረን ብርድ ልብስ ወደኋላ ስለቀረ፣ በደንገተኛ የአየር ለውጥ ምክንያት በጣም ነበር የተቸገርነው፤ ምንም አይነት ምቾት አለ ብሎ ከማሰብ በፊት ስድስት ብርድ ልብሶች ያስፈልጉን

ነበር፡፡ እነዚህን ደግሞ፣ እያንዳንደቸውን፣ በአንድ ዶላር ሂሳብ ካገሩ ተወላጆች ለመግዛት ተገደደን፡፡

የስንቅና ትጥቅ ክፍሉ፣ መቅደላ ለመድረስ የሰባት ቀን ጉዞ ቀርቶናል ሲል አስታወቀ፡፡ ላት እያለን፤ ወደ መቅደላ ስድስት ቀን ነበር ይወስዳል የተባለው፡፡ አሁን ግን አምስት ቀናቶች ከተጓዝን በኋላ፣ እንደ ኮሎኔል ፋይሪ ገለፃ፣ ሰባት ቀን እንደሚቀር ተነገረን፡፡ ዋና አስተርጓሚው ቻርልስ ስፒዲ ግን በሱ ግምት፣ በፍጥነት ከመጓዝ ይልቅ አደጋ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ለማስቀረት መጠባበቂያ ቀኖች ብንጨምር አስራ ሁለት ቀናት እንደሚወስድብን ተናገረ፡፡

የመረጃና የፖለቲካው ክፍል የአቢሲኒያ አለቆችን ገንዘብ በመከፈል ራሱን ወጥሯል፤ ጥሩ ባህሪ እንዲያሳዩ በጉቦ እየደለሉ ነበር፡፡ የኮሚሳሪያቱ ክፍልም ቢሆን አቢሲኒያውያን ይዘው የሚመጡትን ሁሉን ነገር በመግዛት ባተሌ ሆኖ ነበር፡፡

ሰማይ ያቀፈ በሚመስለው እምባቸው የሚኮሩት የአቢሲኒያ አለቆች እንደ ባህር አሳ ሙልጭልጭ የሚሉ ነበሩ፡፡ ከዚህ በፊት፣ የሚወዱት፣ አዲስ ብልጭልጭ የሚል ማር ተሬዛ የተከፈላቸው ቢሆንም፣ ጦሩ መካዝኖችን ትቶ እንደሄደ፣ ወዲያውኑ ተጨማሪ ሥጦታዎች በመጠየቅ ማንጎራጎር ጀመሩ፡፡ ተጨማሪ ክፍያ ተልኮ የሰዎችን ስግብግብ ባህሪ በሚያረካ መንገድ እንዲከፈልና የነበረው ስህተት እንዲታረመ ተደረገ፤ አለበለዚያ፣ በማግባባት ሰላም መፍጠር ካልተቻለ ደግሞ፣ የጉልበት ወይም የሀይል ሥራም ተሠራ፡፡

ሜጀር ግራንትና ካፒቴን ሙር ወደ ዲልዲ ተላኩ፤ ምክንያቱም የተፈጠረው ችግር በራሱ እልባት ማግኘት የሚችል አልነበርም፤ ጉዳዩን በጊዜ እርምጃ ካልወሰዱበት ወደ ከፋ ደረጃ የሚወሰድም ነበር፡፡

የፖለቲካ መኮንኑ ኮሎኔል መርዌዘር፣ በሙል ሥልጣንና ግዴታ፣ የከረኛውን የወልደየሱስን ፍላጎት ለማርካት ሀላፊነት ተሠጥቶት ነበር፡፡ ወልደየሱስ፣ ምንም እንኳን ከናፒየር ጋር ዳቦ ተቋርሶ ቃል ቢገባና ቢምልም፣ ቃል ከገባበት ሁኔታ እየራቀ ነበር፤ እኛ ቦታውን ጥለን ከመጣን ወዲህ፣ የሱ ፍላጎት፣ ካደረገው ስምምነት እየጨመረ እየራቀና ልዩነቱም የከፋ ደረጃ ደርሶ ጠብ እስከሚያነሳ ድረስ ነበር፡፡

እንደሚባለው ከሆነ፣ የናፒየር መልከተኞች ተማርከው በደል እየደረሰባቸው ነበር፤ መልከተኞቹ ሳይተባበሩ ድርቅ ካሉ ይሰለቡ ነበር፡፡ ወልደየሱስና ወንድሙ፣ የራሳቸውን ሰዎች ምንም አይነት ነገር ለሽያጭ እንዳያቀርቡ መከልከላቸው የማያጠራጥር ነገር ነበር፡፡ የአገሩ ተወላጆች ለእንግሊዝ ሠራዊት ጓዝ እንዳያመላልሱ፣ ወይም የሚሸጥ ነገር ይዘው፣

ከመሸከ እስከ አፃላ በነሱ ግዛት በዋጀራት በኩል ባለው መንገድ እንዳያልፉ መከልከላቸው የሚያከራከር አልነበረም።

ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ለጦሩ በየቀኑ ያሚያስፈልገውን ቀለብ ማመላለሱን በሀገሩ ተወላጆች እንዲሆን ወሰኖ ስለነበር፣ እንደዚህ አይነቱ መሰናከልና መከልከል፣ ቀዳሚው ጦር ላይ ከባድ ችግር እንደሚያሰከትል ግልፅ ነው። እያንዳንዱን ትንንሽ እለታ መቅጣቱ ለኛ የሚበጅ ነገር አልነበረም፤ የተገላቢጦሽ ጉዳት ነው የሚያስከትለው። እያንዳንዱ ገዥ፣ በሰማይ ጠቀሰ አምባው ላይ ተቀምጦ፣ ራሱን ከሌሎች ማለትም ከከፍተኛው ዋግሹም ወይም ከትግሬው ልዑል የማያንስ አድርጎ ነው የሚያየው።

የዚህ አይነቱ ስሞታ፣ ጉዳዩን ሰማረጋጋት ለተላከው ኮሎኔል መርዌዘር በግልፅ ላይነገር የቀረ አልነበረም።

በሳንታሬ ቆይታችን፣ በሁለተኛው ቀን፣ ከረፋዱ አምስት ሰአት ላይ፣ በኮረብታዎች ከፍታ ቦታ ላይ፣ በብርድ እየተንቀጠቀጡ እንደ ጥላ የቆሙት ጠባቂዎች፣ በጭጋጋማው ረፋድ ከምዕራብ አቅጣጫ የታጠቁ ሰዎች ሲቃረቡ አይተው የማስጠንቀቂያ ተኩስ ጀመሩ። ወዲያውኑ፣ ቴዎድሮስ ከ50ሺ ሰው ጋር እየመጡ ነው የሚል ወሬ ይሰራጭ ጀመር፤ እንዲህ አይነቱ ጭምጭምታ ሳንታሬ ከመጣን ጀምሮ ጠንከር ያለ ነበር።

የመጀመሪያው የማስጠንቀቂያ ተኩሰ እንደተተኮሰ፣ በቀኑ ተረኛ የነበረው መኮንን፣ ኮሎኔል ፍሬዠር፣ ወደ መጠበቂያ ቦታዎች በመጋሰብ የሚመጡትን እንግዶች በቅርብ መመልከት ጀመረ፤ ከዚያ በኋላ፣ እየተቃረቡ ያሉት ሰዎች ወዳጆች ስለነበሩ ጠባቂዎች ተኩሱን እንዲያቆሙ ነገረ። ዋናው የዕዝ ጽ/ቤት፣ እነዚህ ሰዎች መምጣታቸውን ያውቅ ነበር። የዋግሹም ጎበዜ ጦር አዛዥ፣ ደጃዝማች መሸሻ፣ ሰር ሮበርት ናፒየርን ለመገናኘት በነጋታው እንደሚመጣ፣ መንዚንጀር፣ የደጃዝማች መሸሻን ውሳኔ በሚመለከት ለሰር ሮበርት ናፒየር ብዙ መልከተኞች ልኮ ነበር።

የሲንዲ ፈረሰኞችና የእግረኛ ጠባቂዎች ካምፑን ለማስጠንቀቅ በተኮሱበት ጊዜ፣ በካምፑ ያለው እግረኛ ወደፊት በመገስገስ፣ መጣ የተባለውን ጠላት ለመግጠም በውጊያ መሰመር እያመሩ ነበር። ኮሎኔል ፍሬዠር በወቅቱ ባይደርስ ኖሮ፣ ውጤቱ ወደ ወዳጅ ካምፕ ያለምንም ጥንቃቄ በመዝናናት በሚመጣው የአገሬው ፈረሰኛ ላይ ጉዳት ከማድረሱም በላይ፣ የእንግሊዝ ጦርና 40ሺ ሰራዊት ያለው የዋግሹም ጎበዜ ጦር በተፃራሪነት ይሰለፉ ነበር። በዚህም፣ ዋግሹም ጎበዜ የማታለል ሥራ ተሰራብኝ በማለት ያለምንም ጥርጣሬ ከቴዎድሮሰ ጋር ግምባር በመፍጠር የሰዎቹን ደም ይበቀል ነበር። በዚህ ሁኔታ ደግሞ፣ የእንግሊዝ ሠራዊት፣ ከፊት ለፊቱ ቴዎድሮሰ ከ30ሺ

ሰዎቻቸው ጋር፣ ዋግሹም ጎበዜ ከ40ሺ ሰዎች ጋር ከኋላና ከጎኑ ይከቡት ነበር፡፡

የአቢሲኒያው ጄኔራል መምጣቱ በጠቅላይ ዕዙ ሲታወቅ፣ በታምቡርና በዋሽንት እማካኝነት የየሬጂመንቱ ወታደሮች ወደ ዋና ዕዙ ቦታ እንዲመጡ ተደረገ፡፡ ወታደሮቹም፣ የፀሀይ ባርኔጣቸውን የሚሸፍን ንፁህ ልብስ አልብሰው፣ ነጭ ጓንት አደረጉ፡፡ የ3ኛው ቀላል ፈረሰኞች ቡድን ወደ ሰር ሮበርት ድንኳን አመራና፣ ወደኋላ በመዞር ፊትለፊቱን በማየት ተሰለፈ፡፡ ሁሉም፣ በደንብ የታጠበውን ባለ ብርማ ቀለም ዩኒፎርማቸውን ለብሰዋል፡፡ መኮንኖቻቸው ጥሩ ፈረሶቻቸው ላይ ተፈናጠው ከቀረቡ በኋላ፣ ጥቂት ፈረሰኞች እንዲያጅቧቸው አድርገው መሸሻን ለመገናኘት ገሰገሱ፡፡ በዚህ መሀል፣ አራት ሬጅመንቶች ከነመሳሪያቸው ወደ ካምፑ ምዕራባዊ ዳርቻ ከተራመዱ በኋላ በመስመር ተሰለፉ፡፡ ሰዎቹ በዛ አቅጣጫ ነው የሚመጡት ስለተባለ፣ ሁሉም፣ በጉጉት በግራችን በኩል ወደሚገኙት ከፍታ አናቶች አቅጣጫ ነበር የተመለከቱት፡፡

ግማሽ ሰአት የሚሆን ሊገባደድ ሲል፣ የፈረሰኞች ረዥም መስመር ኮረብታው ላይ ብቅ አለ፡፡ ትንሽ ቆም አሉ፣ በዚህን ጊዜም፣ ከታች እንግዳ የሆነውን ካምፕ፣ በውስጡ ያሉትን በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችንና እንስሶችን ከመረመሩ በኋላ፣ ሁሉም ፈረሰኞች ቁልቁለቱ ከበድ ባለው መንገድ በኩል ወደታች መውረድ ጀመሩ፤ በዚህ ገደላማ ኮረብታ፣ ልክ ደልዳላ ቦታ እንደሚጓዝ በርጋታና በዝግታ እየወረዱ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ቀጥ ያለው ቁልቁለት ወጣ ገባ ያለና በትልልቅ አለቶችና ሸካራ ድንጋዮች የማይመች ቢሆንም፣ ምንም አይነት የማጉረምረም ወይም እርስ በርስ የመጋፋት ምልክት አይታይም፡፡ እርስ በርሱ ሳይገፋፋና፣ በቡድን ተጠጋግቶ ሳይደናቀፍና በየቦታው ሳይበታተን፣ ማንም የአውሮፓዊ ፈረሰኛ እንደዚህ ማድረግ አይችልም ነበር፡፡

የመሸሻ ጦር አሰላለፍ በጣም የሚያስደንቅ ነው፤ ምንም እንኳን የመሬቱ ወጣ ገባነት አንዱን ሰልፍ ከሌላው በሃምሳ ጫማዎች አበላልጦት ቢታይም፣ በሚደነቅ ሁኔታ ሥርአትና ደረጃውን የጠበቀ ነበር፡፡ የኮረብታዎቹ ስር እንደደረሱ፣ አቆሙና በሰልፍ መስመር ሰሩ፡፡ የእንግሊዝ መኮንኖችና አጃቢ ወታደሮቻቸው የአቢሲኒያውን ጄኔራል ከበቡት፤ ከዚያም፣ ልክ ካምፑንና ከፍታ ቦታውን የሚያለያየውን ትንሽ ወራጅ ውሃ እንደተሻገረ፣ መድፈኛው የክብር ተኩስ መተኮስ ጀመረ፤ ይህ ደግሞ ያገሩን ፈረሶች እንዲደነብሩና ሰልፉን እንዲያበላሹ አደረጋቸው፡፡

መሳሪያ የያዙት ሬጅመንቶች ለተኮፈሰው ጄኔራል ሰላምታ ከሠጡ በኋላ፣ ከተወላጆቹ ጦር ፊት ለፊት ቀደም በማለት መራመድ ጀመሩ፡፡ ወታደራዊ

ባንዱ፣ "ጌሪ አውን" የተባለውን ሙዚቃ መጫወት ጀመረ፤ ይህም ጠየም ያሉትን ወታደሮች፣ ሙዚቃው ከወታደራዊ ሁኔታው ጋር አሰደሰቷቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የናፒየር ድንኳን እስከተተከለበት ሥፍራ ደረሰ ተጓዙ፤ የእንግሊዝ ወታደሮች በአራት ማዕዘን ቅርፅ ከፍት ቦታ ሲፈጥሩ፣ መሸሻ ወደ ናፒየር መቀበያ ከፍል እንዲሄድ ተደረገ፡፡ የእንግሊዙ ጀኔራል ከድንኳኑ ወጣ፤ ወዲያውኑ፣ ሁለቱ ጀኔራሎች ተቃቀፉ፡፡

ጀኔራል መሸሻ መካከለኛ ቁመት ያለው ሰው ነው፤ ዕድሜው ወደ ሰላሳ አምስት ይሆናል፤ ፊቱ፣ ደግነት መልካምነት የሚያሳይ ገፅታ አለው፤ የብልህነትም ሁኔታ ያንፀባርቃል፡፡ ከሀር የተሠራ ቀሚስ ለብሷል፡፡ የለበሰው ሸሚዝና ሱሪው ላዩ ላይ ቅርፃቸው ወጣ ባሉ ቀሰም ባላቸው ምስሎች ያጌጠ ነው፤ አንገቱም ላይ እንደ እንቁ የመሰሉ ብጫማ ቀለም ያላቸው መቁጠሪያ የመሰሉ ሀብሎች አድርጓል፤ ጭንቅላቱ ላይ ደግሞ፣ በወርቅ ጥምዝ የተሠራ ብዙ ቀሰማት ያለው የጠርሙስ ጌጦች የተሰኩበት እከሊል የመሰለ ነገር አድርጓል፡፡ በምራባዊ ዋድላ ሰፈር ባመፁ ገበሬዎች ላይ የተሳካ ዘመቻ አድርጎ መመለሱ ነበር፤ ይህ ጥምዝ የራስ ጌጥ ከመሀሉ ላይ ቀንድ ተደርጎበታል፤ ያም የአሸናፊነት ምልክት ነው፡፡ ይህ ከድል በኋላ ቀንድ ማድረግ ከመፅሐፍ ቅዱስ የፃድቃን ቀንድ ከሚለው የተወሰደ ነበር፡፡[111]

የአቢሲኒያውያኑ ሀይል በግምት ወደ 800 ፈረሰኞች ነው የነበረው፤ እነዚህም ከዋግሹሙ ምርጥ ወታደሮች የተውጣጡ ነበሩ፡፡ ሁሉም ጠቆር ያሉ ያገሩ ተወላጆች ናቸው፤ አንድ አይነት አለባበስ፣ ከፊቱ ላይ ጥለት ያለው እጀ ጠባብ ለብሰዋል፡፡ የሚያንፀባርቅ አምባር ከንዶቻቸው ላይ፣ አንገታቸው ላይ ደግሞ ብጫ ቀለም ያላቸው መቁጠሪያ በመሠሉ ነገሮች የተሰሩ ሀብሎች አድርገዋል፤ እግራቸውም ላይ ቢሆን አልቦ አድርገው ነበር፡፡ እያንዳንዱ ወታደር ሁለት ጦሮችና ከበሬ ቆዳ የተሠራ ጋሻ ይዟል፤ ግማሽ የሚሆኑት በእሳት የሚለኮሰውን ጠመንጃ ታጥቀዋል፡፡ አንዱም ፈረስ የፈረሰ ጫማ አላደረገም፡፡

የእንግሊዙና የአቢሲኒያው ጀኔራል ወድ ድንኳኑ ውስጥ ከገቡ በኋላ የሆነው ነገር አይታወቅም፡፡ አለዚያም ማወቁም ጠቃሚ አይሆንም፡፡ የንግግራቸው ፍሬ ነገር የሚሆነው፣ ያለጥርጥር፣ ናፒየር ለጎበዜ መልካም ምኞቱን መግለፅ፤ በተራው ጎበዜ ለናፒየር መልካም ምኞት መግለፅ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ መሸሻ ቴዎድሮስ የሚዋጋ መሆኑን ያለጥርጥር የሚያምንበት ነገር መሆኑን ገለፀ፡፡ ይህ የእንግሊዙን ጀኔራል የሚያረካ መልስ እንዲያገኝ

---

111 መዝሙረ ዳዊት ቁጥር 75፣ "የከፉዎችን ሁሉ ቀንድ እሰብራለሁ፤ የፃድቃን ቀንድ ግን ከፍ ከፍ ይላል፡፡"

ነው ያደረገው፡፡ መሸሻ ቴዎድሮስን በጣም እንደሚፈራው ገለጠ፤ ይህን ደግሞ፣ አስቀድመን፣ እሱ ለናፒየር ከመንገሩ በፊት የገመትነው ነገር ነበር፡፡ ከዛ በኋላ፣ መንዚንጀር፣ መሸሻ፣ ስፒዲና ተሲገር ከሰር ሮበርት ጋር ትንሽ (ራም) አረቄ የመሰለ መጠጥ እንዲጠጡ ተጋበዙ፡፡

ንግግሩ ካለቀ በኋላ፣ መሸሻ የፈረስና ጥንድ አፈሙዝ ያለው ጠመንጃ ስጦታ ተሰጠው፤ ጠመንጃው፣ ወደኋላ፣ የሚኮራበት ነገር የሆነው፡፡ ፈረሱም ቢሆን ያገሩ ተወላጅ ወታደሮችን አድናቆት አግኝቷል፡፡

የደጃች መሸሻ ጋሻ፣ በአንድ ከፍ ያለ ትውልድ ባለው ወጣት ነው የተያዘው፤ ፍፁም ወጣት አዶኒስ[112] ነበር፡፡ በጠይም ፊቱ፣ በጣም መልከ መልካም ሆኖ፣ በአድሜም ሆነ በመልክ የቀድሞ ባሮናች ጦርና ጋሻ ከሚይዙ ተላላኪዎች አይለይም፡፡ የመሸሻ ጋሻ ከልዑል ካሳ ጋሻ ጋራ ይመሳሰላል፡፡

ከነዚህ ሰዎች ስለ አፄ ቴዎድሮስ ጥንካሬና ሀይል ግንዛቤ ማግኘት ችለናል፡፡ የቴዎድሮስ ወታደሮች ከመሸሻ ወታደሮች በትንሹም ቢሆን በተሻለ ሁኔታ ከታጠቁ፣ መቅደላን ለመያዝ የእንግሊዝ ሠራዊት ከፍተኛ ሀይልና ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የተሻሉ ናቸው ብሎ ለማመን ደግሞ በቂ ምክንያት ነበረ፤ ምክንያቱም፣ ቴዎድሮስ፣ ካገሩ ባላባቶችና መሳፍንቶች ጋር በሚያደርጉት ጦርነት ሁልጊዜ አሸናፊ ነበሩ፡፡ ለማንኛውም፣ ስለቴዎድሮስ ሁሉም ነገር ሚስጥራዊ ነው የነበረው፡፡ ሰላዮች ወደ ካምፑ ሲመጡ፣ ለለሳቸው የሚወራው በሙሉ የተጋነነ ስለነበር ትክክለኛውን ሁኔታ ማወቅ አይቻልም ነበር፡፡ ከእስረኞቹ የሚላኩት ደብዳቤዎች ቢሆንም ድፍን ያሉ ስለሆኑ፣ ለጀማሪ ዲፕሎማት ስለመቅደላና አካባቢው በቂ ግንዛቤ አይሰጡም፡፡ በዚህ ሁኔታ፣ ጄኔራል ናፒየር ወደፊት መግፋት እንጂ ሌላ አማራጭ አልነበረውም፤ በዚህም ተስፋ ያደረገው ሁሉም ችግሮች በሚመጡት ቀናት አልባት እንደሚያገኙ፣ ሁሉም የሚወሩ ወሬዎችና ጥርጣሪዎች ደግሞ ጭራሹን እንደሚያቆሙ ነበር፡፡

በዚህ ቀን ማምሻውን፣ ጄኔራል ስታቬሊ ከ33ኛው እግረኛ፣ ፑንጃብ ቃኝዎች ሶስት ኮምፓኒ፣ ከተዊስ ከባድ መሳሪያ ከፍል፣ የ3ኛው የህንድ ተወላጆች ፈረሰኛ ካምፓኒ፣ የሮኬት ከፍሉ የባህር ሀይል ብርጌድ፣ ከአውሮፓ እግረኞች ሌላ ሬጅመንት ማለትም 46ኛው እግረኛ፣ የ3ኛው ድራጎን ጋርድስ (አውሮፓውያን) እና ከቤሉቺዎች ግራ ከንፍ ጋር በመሆን ዋድላ ደረሰ፡፡

---

112 በግሪክ አፈ ታሪክ፣ አዶኒስ በጣም መልከኛ ወጣት ስለነበር፣ በአማልክቷ በአፍሮዳይቲና በፐርሶፎኒ ከሚያስጨንቃቸው የማስታወስ ዓይነቶች ምንም በምትኖረው ሌላ እማልክት ፐረስፎን የሚወደድ ነበር፡፡ ሲሞት፣ የአማልክቶቹ አለቃ ዙስ፣ ወጣቱን ወደ ምድር እየመጣ ከአፍሮዳይቲ ጋር፣ ከታች ደግሞ ከፐረስፎን ጋር እኩል ጊዜውን እንዲያሳልፍ ፈቀደለት፡፡ አፍሮዳይቲ የፍቅር አምላክ ተብላ ነው የምትታወቀው፡፡



*ሜጀር ጄኔራል ቻርለስ ስታቬሊ*
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ሳንታሬ በደረስን በሶስተኛው ቀን፣ ፣ኛው ብርጌድ ካምፕ ነቅሎ አስራ ስድስት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ ጋዞ እንቅስቃሴ ጀመረ፡፡

የዋድላ ከፍታ ከኢሊኒዮስና ከኔብራስካ ሜዳዎች ጋር ይመሳሰላል፤ ነገር ግን፣ በአቢሲኒያው መሬት፣ ድንጋዮች እሁንም እሁንም ከአፈሩና ከሳሩ በላይ ፈጦ እያሉ ይወጣሉ፡፡ ብዛት ያላቸው አረንጓዴ የለንዴ እርሻ ቦታዎች እለፍን፤ በጎናቸው ደግሞ፣ ለእጨዳ የደረሱ የጤፍ እርሻዎች ነበሩ፡፡ በዚህም በዚያም፣ ትንንሽ መንደሮች ይታያሉ፤ መንደሮችም በቁጥቋጦ አጥሮች የተከበቡ ነበሩ፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን የሚያስደስት ነፋሻ አየር አለ፤ ይህ ደግሞ ባናታችን ላይ ከሚወርደው የፀሀይ ጨረር ጋር ሊኖር የሚችለውን ሙቀት ይቀንሰዋል፡፡

የኛ አስተርጓሚ፣ የቀድሞው የቴዎድሮስ ባሻ፣ ቻርለስ ስፒዲ፣ በየመንደሩ እየዞረ እህልና ዶቄት እንዲገዛ በናፒየር ታዘዘ፡፡ ሚስተር ስፒዲም እኔን አብረን እንድንሄድ ጋበዘኝ፤ በንግግሩም፣ በእንግሊዝ ዶላር ያልተበከሉ ሰዎችን ሁኔታ ማየት እንድችል ነበር፡፡ እኔም ጥሪውን በደስታ ተቀበልኩኝ፡፡

እኔና ካፒቴን ስፒዲ፣ መጀመሪያ የገባንበት መንደር ዎጣ ይባላል፤ የእንግሊዝ ሠራዊት ባለፈበት መንገድ፣ በግራ በኩል፣ ከሶስት ማይሎች ርቀት ላይ ይገኛል።

የኛን መምጣት ሲያዩ፣ ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ ሽማግሌዎች ወደፊት መጥተው እጅ ነሱ። ስፒዲም የተለመደውን ሰላምታ፣ በአማርኛ፣ "እንደምን ዋላችሁ።" በማለት ጀመረ። እነሱም፣ በእጆቻቸው ሶስት ጊዜ ራሶቻቸውን በመንካት ሰላምታ ሲሰጡ፣ ስፒዲም፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያዊ ባህል ሰላምታውን መሰሰ።

የሰውነታቸው እንቅስቃሴ፣ እኔ እንደተረዳሁት፣ የሚያሳዩት፣ በመፅሐፍ ቅዱስ እንደተፃፈው የመጋበዝ ምልክት ነበር።

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አስራ ስምንት እንደተፃፈው፣ "አቤቱ በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ።"

"ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ፤ እግራችሁን ታጠቡ፤ ከዚህችም ዛፍ በታች ዕረፉ፤ ቍራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ፤ ልባችሁንም ደግፉ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ፤ ስለዚህ ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና።"

ጓደኛዬም በግብዣው ተስማምቶ ሁሉም ነገር በጣም ጥሩ ነው ብሎ ተናገረ።

እኛም፣ ከሚያምር እርንጓዴ የኮሶ ዛፍ ሥር ተቀመጥን፤ ከፊት ለፊታችንም፣ ዳቦ፣ ቅቤ፣ ወተት፣ የበግ የኋላ እግር ስጋ አቀረቡልን። ከዛፉ ስር፣ በኛ አጠገብ ቆመው፣ ስንበላ መጥፎ መንፈስ እንዳያየን በጋቢ ጋረዱን። በላን። ወተቱ ጣፋጭ ነበር፤ ዳቦውም ቢሆን በጣም ጥሩ ነበር፤ ሥጋው ደግሞ ለስለስና በርከት ያለ ነበር።

በድንገት የተዘጋጀው ምግብ ከተነሳ በኋላ፣ ሴቶች በቆሎና ዶቄታቸውን ለሽያጭ ይዘው መጡ። እኛም ከብር የተሰሩ ዶላሮችን በሚያጓጓ መልክ ከፊት ለፊታችን ዘርግተናቸው ነበር። መጀመሪያ የገዛነው ዶቄት ስድስት ፓውንዶችም አይሆንም ነበር፤ ግን አንድ ዶላር ከፈልንበት፤ ከዚህ አነስተኛ መጠን በመነሳት፣ ቀስ በቀስ ከብደቱ እየጨመረ በአንድ ዶላር ከፍተኛ መጠኑ አስራ ሶስት ፓውንድ ድረስ መግዛት ቻልን። የእህልና የዶቄቱ ከምር ቀስ እያለ እየጨመረ በመምጣት የግብፆችን ፒራሚድ የሚመስል ቅርፅ መያዝ ጀመረ። ከዚህ በተጨማሪ፣ ስልቻዎች፣ በቅሎዎችና መጫኛዎችም ገዛን።

ዎጣን ለቀን ከመሄዳችን በፊት፣ ካፒቴን ስፒዲና እኔ 4ሺ ፓውንድ ዶቄትና ሶስት ሺ አምስት መቶ ፓውንድ እህል ይዘናል። ለቀን ስንሄድ፣ በነዚህ ደግ የመንደሩ ሰዎች ልባዊ ምርቃን ወረደልን።



*ካፒቴን ሰፒዲ (ባሻ ፈለቀ)*
(ዋቢ. መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ከዎጣ ወደ ማይ አይኒ ሄድን፤ በዚህም የካፒቴን ሰፒዲ የሚታወቅ ታሪክ ያልተለመደ አትኩሮትና ክብር እንዲፈጠር አደረገ፡፡ እሱ ሲንቀሳቀስ ሁሉም ባንድ ጊዜ ከፊት ለፊቱ ይርቃሉ፤ በቀልድ መልክም፣ ይህ የእናክ[113] ልጅ፣ ባሻ ፈለቀ ማድረግ የሚችለውን ነገር ለማሳየት በአንድ ጠንካራ እጁ ከወጣቶቹ አንዱን አፈፍ አድርጎ ያነሳ ነበር፡፡

የማይ አይኒ አለቃ ነገር የተለየ ነበር፡፡ ለረዥም ጊዜ በሚያከሳ በሽታ ስለሚሰቃይ አፅም ነበር የሚመስለው፡፡ በብዙ ሰላምታዎች፣ እንኳን ደህና መጣችሁ ብሎ ተቀበለን፡፡ በዙሪያው፣ ብዛት ያላቸው የሚወዛወዙና የሚስቁ ልጃገረዶች ነበሩ፡፡ ወጣት ልጆች የኛን ድምፅ ሲሰሙ፣ ከየመንደራቸው እየተሰባሰቡ መጡ፤ እንደ ብዙ ዳዊትና ዮናታኖች፣ እርስ በርስ ከንዶቻቸው

[113] በመፅሐፍ ቅዱስ የሚጠቀሱ ግዙፍ ሰዎች (ጃይንቶች)

ላይ ተደጋግፈው ነበር:: በአቢሲኒያ፣ ከዚህ ቀን በፊት፣ እንደዚህ የሚያስገርም ለይታ አይቼ አላውቅም:: እርጎ የተሞላባቸው ምንቸቶችና መያዣዎች ፊት ለፊታችን ቀረቡ፤ እንደ ክሊዎፓትትራ ግርማ ያላት አንዲት ሴት፣ እኔን ለማክበር፣ ስፒዲ እንደነገረኝ ከሆነ፣ ግሬራውን ከአፌ አስጠግታ እሷ እንደያዘችልኝ እርጎውን እንድጠጣ ጠየቀችኝ::

ከዚህ መንደር ማግኘት የቻልነው፣ 40 በቅሎዎች፣ 30 ፈረሶች፣ 1700 ፓውንድ ዶቄት፣ 3ሺ ፓውንድ እህል፣ 300 ዳቦ፣ 75 ስልቻ፣ እና 100 ክንድ የሚረዝም የጠፍር ገመድ ነበር:: አመሻሽ ላይ የእንግሊዝ ሠራዊት ያለበት ካምፕ፣ ጋዞ ደረስን::*(በዚህ ጊዜ ስፒዲን በማገዝ ለብሪታንያ መንግሥት ያደረግኩት አገልግሎት ታላቅ ነበር:: ግን፣ ለመናገር አዝናለሁ፣ ታላቁ የብሪታንያ መንግሥት አመስግኖኝም አያውቅም፤ ቢያንስ ቢያንስ በአቢሲኒያ ዘመቻ የተሰለፉ ጀግኖች የተሠጣቸውን ሜዳልያ ሊሰጡኝ በተገባ ነበር:: ይህን ጉዳይ፣ እኔ፣ በብሪታንያ መንግሥት በኩል ያልተለመደ መዘንጋት አድርጌ ነው የወሰድኩት:: እናም ለዚህ ታሪክ ፀሀፊ በጣም ከበድ ያለ በደል ነው የደረሰበት::)*

ጦሩ ከጋዞ ተነስቶ አስራ አምስት ማይሎች ርቀት ወደሚገኘው ወደ አብደቁም ተጓዘ::

የዚህ አካባቢ የአገሩ ሁኔታ በጋዞና በሳንታሪ ካየነው ጋር ይመሳሰላል፤ የሚለየው ነገር ቢኖር ይኼኛው ትንሽ ደልዳላነት አለው::

በአብደቁምና በመቅደላ መሀከል ተራብን የሚሉ ሰዎች ዘገባ ከመጠን በላይ ነበር:: እንደሚባለው ከሆነ፣ ቴዎድሮስ አገሩን በሙሉ አቃጥለውታል፤ ያለ የሌለ እህሉን ይዘውት ሄደዋል፤ ስለዚህ፣ የናፒየር፣ በመላ የተዘጋጀው ዕቅድ፣ መጨረሻው ወደ ድንገተኛ አደጋ የሚያመራ ይመስላል:: ነገር ግን፣ ብዙ መሠረት የሌላቸው ወሬዎች ሲሰራጩ ስለነበር፣ ሰዎች በአቢሲኒያ ስለሚወራ ማንኛውም ነገር ሙሉ እምነት አልነበራቸውም::

ያም ሆኖ የምግብ ራሽን ያነሰ ነበር፣ የነበረንም ስንቅ ቢሆን መገባደድ ከጀመረ ቆይቷል:: ለአንድ ሳምንት፣ ቡና፣ ስኳር፣ ድንች፣ አልኮል፣ ቅጠላ ቅጠልና አይብ አልነበረንም:: በጣም ባነሰ ቀለብ ነበር የምንኖረው፤ በቀን፣ አንድ ፓውንድ ሥጋ፣ ስኳር የሌለው ሻይ፣ አስር አውንስ ዶቄት፣ አራት አወንስ ሩዝ፣ እናም ግማሽ አወንስ አሞሌ ጨው ነበር:: ሠራተኞቻችን ደግሞ፣ ለወታደሮች ከሚታደለው ራሽን ግማሽ ነበር የሚሰጣቸው:: ፈረሶቻችንም ቢሆኑ፣ በስምንት ፓውንድ ሳርና በአራት ፓወንድ ገብስ ነበር የሚኖሩት:: በቅሎዎች ደግሞ፣ አራት ፓውንድ ሳርና ሶስት ፓውንድ ገብስ ነበር የሚሠጣቸው:: የወደፊት ሁኔታው በጣም ጨለም ያለ ነበር:: በሁለት ተጨማሪ ቀናት የነበረውን ሁሉንም ቀለብ አንጨርሰዋለን:: የስንቅ ክፍሉ በየቀኑ ተጨማሪ ስንቅ ካላገኘ፣ በእርግጠኛነት ረሃብ ይገባል፤ የቀረን ነገር

ቢኖር የነበሩ ከብቶቻችን መግደል ነው፡፡ እንደዛ ከሆን ደግሞ ተጨማሪ ቀለብ ከአንጣሎ እስከሚመጣ ድረስ ለአንድ ወር የሚሆን ቀለብ ይኖረናል፡፡ ይህ ሀሳብ ግን ምንም የሚያስደስትም አልነበረም፡፡

በሁለተኛው ቀን፣ ጦሩ ከአብደቁም ወደ ስንዲ ተሻገረ፤ ያም የሶስት ማይሎች ርቀት ብቻ ነው የነበረው፡፡ የሰር ቻርለስ ስታቨሊ 2ኛው ብርጌድ ማምሻውኑ አብደቁም ደረሰ፡፡ ስለዚህ በሁለቱ ብርጌዶች መሀል የሶስት ማይሎች ልዩነት ብቻ ነው የነበረው፡፡

የኀበዜ እንት፣ ጄኔራል መሸሻ፣ ከሰአት በኋላ ወደ ናፒየር መጣ፡፡ ሶስት መቶ በሚሆኑ ፈረሰኞች ታጅቦ ነበር፡፡ ከደረሰ በኋላም፣ ጄኔራል ናፒየርን፣ 6ሺ ፓውንድ የሚሆን ዶቄትና እህል የገዛ መሆኑንና ያንኑም ወደ ካምፑ በቀጥታ የሚልከ መሆኑን ነገረው፡፡ ይህ በጣም የሚያረካ ዜና ነበር፡፡

ቀኑ መሽቶ ስለነበር፣ መሸሻ፣ ከካምፑ ብዙም ሳይርቅ ከፍ ያለ ቦታ ላይ ወዳለ መንደር በመሄድ አብረውት ከነበሩ ሰዎች የተወሰኑትን በመንደሩ እንዲቆዩ መራ፡፡ ያንን መንደርም ትቶ ከቀሪው ጦሩ ጋር ለመደባለቅ ሶስት ማይሎች በሰሜን አቅጣጫ ሲጓዝ፣ ከጄኔራል ስታቨሊ ጠባቂ ዘቦች ጋር ድንገት ይገናኛል፡፡ ጠባቂ ወታደሮቹም፣ አንድ አስር አለቃና የ3ኛው ቀላል ፈረሰኛ አራት ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ወታደሮች መሸሻን አያውቁም፣ ስለሱ ከዚህ በፊት የሰሙ መሆናቸው ያጠራጥራል፡፡ ነገር ግን፣ በየቀኑ ድንገት አደጋ ይጥላል ስለሚባሉት ቴዎድሮስ ይሰሙ ስለነበር፣ ይህ በድንገት ወደነሱ የሚገሰግሰው ጦር ወይ ንጉሡ ራሳቸው ናቸው አለዚያም የንጉሡ አሳሽ ጦር ነው ብለው አሰቡ፡፡ ፈረሰኞቹ ወደነሱ ሲገሰግሱ ሲያዩ፣ ለማስጠንቀቅ መጮህ ጀመሩ፡፡ ነገር ግን፣ ማንም ሰው በድንገት በጠባቂ ዘቦች ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ፈረሰኞቹ በግትርነት ወደፊት ገሰገሱ፡፡ ለወታደሮቹም ይህ ሁኔታ ጥርጣሬያቸውን ያረጋገጠ መሰለ፡፡ እስር አለቃው ተኩስ እንዲጀመር ትዛዝ ሰጠ፡፡ ዘቦቹ ሲተኩሱ ወዲያውኑ ሁለት የመሸሻ ሰዎች አፀፋ ተኮሱ፡፡ አስር አለቃው፣ ወታደሮቹ በሰዎቹ ላይ በተከታታይ እንዲተኩሱ ካዘዘ በኋላ፣ "ወደፊት" በሚል ቃል እንዲያጠቁ ተናገረ፡፡ እነዚህ አምስት ወታደሮች፣ ሃምሳ የሚሆኑ ጎራዴ የያዙ አቢሲኒያውን ላይ ገሰገሱ፡፡ መሸሻ፣ የተፈጠረውን ስህተት በመገንዘብ ሰዎቹ ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ ትዛዝ ሰጠ፡፡ ነገር ግን አጥቂዎቹ ወደኋላ የዘገዩትን እየቆረጡና እየወጉ ነበር፡፡ የቀሩትን ካሳደዱ በኋላ፣ እባረው መያዝ የማይችሉ መሆኑን ሲገነዘቡ፣ እነዚህ ቁጥራቸው እነስ ያለ ጠባቂዎች ሁለት ከገዱሉና ሁለት ካቆሰሉ በኋላ ወደ ምድብ ቦታቸው ተመለሱ፡፡

እንደሚጠበቀው፣ ተኩሱ በሁለቱ ካምፖች፣ በናፒየርና በስታቨሊ መሀል ግርግር ፈጠረ፡፡ 2ኛው ብርጌድ ትጥቁን አንስቶ ከካምፑ ውጭ መሰመር ሰራ፤

3ኛው ቀላል ፈረሰኛ ደግሞ በቅርብ ያለውን ጋራ ተቆጣጠረ፡፡ 4ኛው የአውሮፓ አግሪኛ እና በሎቹዎች ከ፲ኛው ብርጌድ ካምፕ ውጭ ተንቀሳቀሱ፤ በዙሪያው የሚገኝ ሰፊ ቦታ መቆጣጠር የሚያስችል ክፍታ ለመያዝ ነበር፡፡ ሁሉም፣ ለአጭር ጊዜ ቢሆን፣ ተኩሱ በጠባቂዎችና በጠላት መሀከል ነው ብሎ ያመነው፡፡

አስተርጓሚው ሚስተር መንዚንጀር፣ ከሲንዲ ፈረሰኛ የተወሰነ ከፍል ጋር በመሆን ሁኔታውን ለማጣራት ተንቀሳቀሰ፡፡ መሸሻና ሰዎቹ የተጠጉበት መንደር መከላከያ ነበረው፤ አጥሩም በተናደዱ የመሸሻ ሰዎች እየተጠበቀ ነበር፡፡ ሰዎቹም፣ ፈረንጆቹ ተንኮለኞች ናቸው፤ ባንድ በኩል ለአስቃቸው የወዳጅነት ፊት ያሳዩት ለመግደል አስበው ነው በማለት ስላመኑ፣ ወደፊት ወደነሱ ወደሚመጣው የሰንዲ ፈረሰኛ ላይ ከመተኮስ የተቆጠቡት በመከራ ነበር፡፡

በመንዚንጀር በኩል በትግሰት ብዙ ውትወታ ከተደረገ በኋላ፣ መሸሻ ወደ መግቢያው በር መጥቶ የሚለውን ለመስማት ተስማማ፡፡ በቂ ገሰፃና ምክንያቶች ከተሠጡ በኋላ፣ በአቢሲኒያው አስቃ በኩል ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ ተደረገ፡፡ ለሞቱት ሰዎች ቤተሰቦች የደም ካሳ ከፍያ ሶስት መቶ ዶላሮች ተሰጠ፤ ይህም ቤተሰቦቻቸውን የሚያረካ ሆኖ ነው የተገኘው፡፡ የሞቱት ሰዎች፣ ክፍ ያሉ አለቆች ሳይሆኑ ተራ ገበሬዎች በመሆናቸው፣ የደም ካሳው በኢትዮጵያ ቀለል ተደርጎ ነው የሚወሰደው፡፡ የቆሰሉት ሰዎች ወደ እንግሊዞች ሆስፒታል ተወስደው ህክምና ተደረገላቸው፡፡

በሚቀጥለው ቀን፣ ጦሩ ከሰንዲ ተነስቶ ቁልቁል የጀዳን ሸለቆ አቋርጦ እንደገና ወደላይ፣ በተቃራኒው በኩል፣ ወዳለው ወደ ዳውንት ደላንታ ከፍታ ተጓዘ፤ የዚህ ቦታ ከፍታም ከባህር ወለል ፲ሺ ጫማ ነው፡፡

ከሰንዲ እስከ ሸለቆው ድረስ ስድስት ማይሎች ርቀት አለው፡፡ ሸለቆ ማለት ረዥም፣ ጥልቀት ያለው ጠበብ ያለ ቦታ ነው፡፡ ይህ የሸለቆ ጥሩ ገለፃ ቢሆንም፣ የጀዳን ሸለቆ በሁለት አኩል በሆኑ አምባዎች መካከል የሚገኝ ጥልቀት ያለው ቦታ ነው ብዬ ብገልጥ በጣም ጥቂት ሰዎች ነው የጀዳን ሸለቆ ውነተኛ ስፋትና ጥልቀት ሊገነዘቡ የሚችሉት፡፡ መናገር ካለብኝና ከተናገርኩ፣ ከቆምንበት ከዋድላ ጫፍ ከስራችን አፉን ከፍቶ የሚታየው ይህ ሸለቆ የሰላሳ ማይሎች ርዝምት፣ የሶስት ሺ ስምንት መቶ ጫማዎች ጥልቀትና፣ በዋድላና በደላንታ መሀል የሁለት ማይሎች ስፋት አለው፡፡ ስለዚህ ለአንባቢዎች የጀዳ ሸለቆን የውነተኛ ተፈጥሮ መግለፅ ነበረብኝ፡፡ ለብዙዎች ይህ ትክክለኛ ገለፃ እንኳን የሚያሰፈራውን ጥልቀትና ገፅታ በውል ሊያስገነዝባቸው አይችልም፡፡ ስለዚህ ይህንን መግለፅ ደግሞ የኔ ግዴታ ነው ብዬ ስለማምን ስለቦታው በዝርዝር አገልፃለሁ፡፡

ከካምፑ ሁለት ማይል ሳር የበዛበትን አካባቢ ለቀን ሄድን፤ ፊት ለፊታችን ደግሞ በአሳት የተለበለበ የተንጣለለ ቦታ ይጠብቀናል፤ የቴዎድሮስ ወታደሮች የእጅ ሥራ ነበር፡፡ ገራገር የሆነ ዳገታማ ኮረብታ ወጥተን ስንጨርስ፣ ጨለማ የሆነ የቋጥኞች ግድግዳ በዋድላ ተቃራኒ በኩል ይታይ ጀመር፡፡ ወደ አፋፉ ጠጋ ስንል፣ የቴዎድሮስ ካምፕ የነበር ቦታ አገኘን፡፡ ቤት ሆር ነበር፣ ብዙ ጊዜ በጋዜጣዎችም ይጠቀሳል፤ ከታች በጀዳ ሸለቆ መንገድ ሲያሰሩ የንጉሡ ካምፕ በዚህ ቦታ ነበር፡፡

በካምፑ ዙሪያ፣ በማያወላውል ሁኔታ የጦርነት ጭካኔ ኮቴ የሆነ የሚያስፈራ ፅልመት ይታያል፡፡ አሁንም ቢሆን መጠጫ ቦታዎች፣ ለወታደሮች ዳስ ሆነው ተሰርተው የነበሩ ከቢጫ ሳር ጋር የተጠላለፉ የዛፍ ቅርንጫፎች ይታያሉ፡፡ የተመለመሉ የበግና የበሬ አጥንቶች ሜዳውን ሞልተውታል፡፡ ከዚህ ከዚያም ያገሬው ሰዎች የተበጣጠሱ የጥቁር ብልድ ልብስ ብጫቂዎች ይታያሉ፤ ከእንጨት የተሰሩ የጀርባ ማከኪያዎች፣ ከቀንድ የተሠሩ ማንኪያዎች፣ ከቀንድ የተሠሩ ዋንጫዎች፣ የሴቶች ትራሶች እናም ቁጥራቸው በርከት ያለ የቆዳ ሽርጦች ይታያሉ፡፡ በዚህ ቦታም ሴቶቹ እህል የሚፈጩባቸው የድንጋይ ወፍጮ ስባሪዎች፤ የተሰባበሩ የመፍተያ እንጨቶች በየቦታው ተብተነው ይታያሉ፡፡ በካምፑ መሀል ላይ፣ ለኛ፣ ቴዎድሮስ ሰዎቻቸውን እንዴት በጭካኔ ይገዙ እንደነበር ምልከት የሚሆን፣ የተቆረጠ የለው ከንድና፣ በአግድሞሹ የተተረተረ የራስ ቅል አየን፡፡

የአፋፉ ደንበር ስንደርስ፣ ቴዎድሮስ በጠንካራ አለት ላይ ያሉሩት መንገድ ከፊት ለፊታችን ተከፍቶ ጠበቀን፡፡ በዚህ መንገድ፣ የተጓዡ የመጀመሪያው ክፍል በአንድ ጊዜ አለፈበት፡፡ ለመጀመሪያዎቹ መቶ ያርዶች በጣም ቁልቁለት ነበር፤ ሲለካ፣ ከስር አንድ ጫማ፣ ከፍታው ላይ ደግሞ ሶስት ጫማ ነበር፡፡ በዚህ ማለፊያ በሙሉው መንገድ፣ የቴዎድሮስ የመቦርቦሪያ ምልክቶችን ማየት እንችል ነበር፡፡ ይህ መንገድ ለንጉሡ በጣም አድካሚ መሆን ነበረበት፤ ምክንያቱም የተጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ጥራት ያልነበራቸው ከመሆኑ በተጨማሪ እንደ ጎበዜ ያለ ጠላት ከላይ እያንዣበበ፣ ሌላው ጠላት፣ የእንግሊዝ ጦር ከኋላቸው እየገሰገሰ ነበር፡፡ ያገሩ ተወላጆች እንዳሉት፣ ንጉሡ ራሳቸው እንደ ተራ ሰው በጣም ይሰሩ ነበር፡፡ የሥራውን ሁኔታ ለማየት፣ በነጭ በቅሎ ያለማቋረጥ ወዲያና ወዲህ ይመላለሱ ነበር፡፡ አንዳንዴ ሲያበረታቱና ሲያመሰግኑ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲያስፈራሩ፤ አልፎ አልፎም ሲያስገርፉ፣ ካልሆነም ደግሞ ሰው በሞት እንዲቀጣ ትዛዝ ይሰጡ ነበር፡፡ አንደገናም ከበቅሏቸው ይወርዱና ራሳቸው በመስራት፣ ስራ እንዴት መሰራት እንዳለበት ለሰዎቻቸው በምሳሌ ያሳዩ ነበር፡፡ ከአምስት ሳምንታት አድካሚ ሥራ በኋላ፣ ከዋድላ ከፍታ ቁልቁል ወደ ጀዳ፣ ከዛም ወደላይ ወደ ደላንታ

አፋፍ የሰላሳ ጫማዎች ስፋት ያለው የስምንት ማይሎች ርዝመት መንገድ ሠርተዋል፡፡ በዚህ መንገድ፣ ወደ ታች ቁልቁል፣ ከአንዱ አርከን ወደ አንዱ፣ ወደታች፣ አንዳንዴም ቀጥ ያለ ገደል ሲሆን ትንሽ በሚቀረው ቦታ ተጉዘን፣ ከታች ከሸለቆው ወለል ድረስ ወረድን፡፡ ወለሉ ደግሞ በጠጠሮችና ደቦልቦል ባሉ ድንጋዮች ተሸፍኗል፡፡ በጣም ጠለቅ ባሉ ጉድጓድ ቦታዎች ውሀ ይገኝባቸው ነበር፡፡

ከቀኑ ስምንት ሰአት ሲሆን፣ የተጓዡ ቀዳሚ ክፍል እንደገና መንቀሳቀስ ጀመረ፤ ወደላይ ለመውጣት የሚታገሉትን ወታደሮች ፊት ማየት በጣም የሚያሳዝን ነበር፤ በፊታቸው ላይ ተስፋ የመቁረጥና የመከፋት ሁኔታ ይነበብ ነበር፡፡ እነሱ ደረጃ በደረጃ ሲጓዙ መከተል አያስፈልግም፤ ባጠቃላይ በየሃምሳ እርምጃዎች ቆም እያሉ፣ ከቀኑ አስር ሰአት ሲሆን የደላንታ አፋፍ ላይ ወጡ፡፡

ከዚህ ቦታ ሆነን፣ የጦሩ ጓዝ መስመር ከዋድላ ጀምሮ ቁልቁል ሲወርድና ወደላይ ወደላንታ አቀበቱን ሲወጣ በሙሉ ርዝመቱ ማየት እንችላለን፡፡ ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰአት ከሰንዱ ተነስተን መንገድ ብንጀምርም፣ የሚያስደንቀው ነገር፣ የጓዝ መስመሩ የመጨረሻው ክፍል፣ ከቀኑ እስር ሰአት ላይ እንኳን ገና ከዋድላ አልተነቃነቀም፡፡ ጓዛቸው ወደኋላ የቀረባቸው ሰዎች፣ ሌሊቱን ያለ ድንኳን፣ ብርድልብስ ወይም ያለ እራት እንደሚያሳልፉ በአእምሯቸው መዘጋጀት አለባቸው፤ አዛኝ የሆኑ ሰዎች ተገኝተው ለዚህ ቀን ማታ ምግብ ካላካፈሏቸው በስተቀር፡፡

አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን፣ አሊ በአሽናፊነት፣ የኔን ጓዝ ይዞ ከተፍ አለ፡፡ ካርቴን ስዊኒ ሁለት ጊዜ ቢያስቆመውም፣ በመንገዱ ላይ ብዙ የማይሆኑ ሁኔታዎች ስለሚፈጠሩ፣ አረቡ አሊ፣ ሁለቱን ኢጋሰሶች ከለዎቹ ነጥሎ ለትንፋሽ ካልሆነ በስተቀር ምንም ሳያቆም ይዟቸው መጣ፡፡

በአዲሱ ካምፓችን በደላንታ፣ ማምሻውኑ የጓዙ ግማሹ እንኳን አልደረሰም፡፡ ጨለማው ሲመጣ ደግሞ፣ በተጠማዘዘው መንገድ ላይ በመካተን ላይ ያሉ ሰዎች ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ተዋጡ፤ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው በነበረበት ቦታ የሚቻለውን ማድረግ ነበረበት፡፡ ኮርቻዎችን አውርደው፣ ጭነቶችንም አራግፈው፣ በቅሎ ወይም ፈረሶቻቸውን ከጥጋቸው በሚገኝ ቁጥቋጦ አሰረው፣ ከዛፍ ወይም ከቁጥቋጦ ስር በመተኛት በተቻላቸው መጠን ድካማቸውን ለማሳለፍ ሞከሩ፡፡

በሚቀጥለው ቀን ማታ ከመሸ በኋላ ነበር የተወጠረው የጓዝ መስመር ደላንታ አፋፍ የደረሰው፡፡ በሸለቆው፣ እንስሳቶች በቁጥር ሞተዋል፡፡

ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት ተጨማሪ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚሞከር ነገር አልነበረም፡፡ በእጃችን ቀሰብ ወይም ራሽን አልነበረም፡፡ እንደኮሚሳሪያቱ

ሪፖርት፣ 4ሺ ፓውንድ እህል ብቻ ነው የነበረው፡፡ ይህ መጠን በ1ኛው ብርጌድ ውስጥ ለነበሩ 5ሺ እንስሶች ቢከፋፈል፣ ከሰላሳ ስድስት ሰአታት ፆም በኋላ እያንዳንዳቸው ሊደርሳቸው የሚችለው ስድስት ተኩል አውንስ ነበር፡፡ በዚያን ቀን ደግሞ የሰር ቻርለስ ስታቨሊ ብርጌድ ከተጨማሪ 5ሺ እንስሶች ጋር ስለሚመጣ ምንም የሚተርፍ እህል አልነበረም፡፡ ስለዚህ ካፒቴን ስፒዲ የደላንታውን ገዢ እንዲያናግር በአስቸኳይ ተላከ፡፡ የደላንታው ገዥ ሁልጊዜ ለቴዎድሮስ ቀሰብ አልሰጥም በማለት ከሸፍቶች ሁሉ ቀንደኛው ነው የነበረው፡፡ ስለዚህ የሚገዛ ቀሰብ ካለ ስፒዲ እንዲጠይቅ ነው፡፡

የስፒዲ ተልኮ በጣም የተሳካ ነበር[114]፡፡ መቶ በቅሎዎች ከነሙሉ ጭነታቸው ይዞ ተመለሰ፤ የተጫነው እህል ቢገመት ወደ 10ሺ ፓውንዶች ይሆናል፤ ከዚህ በተጨማሪ፣ በሚቀጥለው ቀን ሌላ መቶ ሺ ፓውንዶች የሚሆን እህል እንደሚያገኝ ቃል ተገብቶለታል፡፡

ይህ በርግጥ በጣም የሚያስደስት ዜና የነበረው፤ በተለይም በቴዎድሮስ ተዘርፏል ከተባለ የአገሩ ከፊል ይህን ያህል መገኘቱ፡፡ የደላንታው ገዥ፣ የእንግሊዞችን ጉዳይ ያለማመንታት ተቀብሎታል፤ ስለዚህ ደስታው የጋራ ነበር፡፡ በሚቀጥለው ቀን፣ ሚያዝያ 7፣ ከደላንታ የትተረፈረፈ ነገር ሲመጣ ነው ምስክር የሆነው፡፡ እህል፣ ዶቄት፣ ዳቦ፣ ማር፣ ዶሮ፣ ሳር፣ ገለባ፣ በሬና ፍየሎች ነበሩ፡፡

ሚያዝያ 7፣ ማምሻውን ለረዥም ጊዜ ሊጠበቁ የነበሩት፣ የ45ኛው ሬጅመንት እና የ3ኛው ድራጎን ጋርድስ ደላንታ ካምፕ ደረሱ፡፡

ጦሩ፣ አሁን አንድ ቦታ ስብሰብ ብሏል እናም የተዋጊዎች ቁጥር ወደ 5500 ደርሷል፡፡ የነዚህ ሁለት ክፍሎች ከአንጣሎ እስከ ደላንታ ያደረጉት ፈጣን ጉዞ፣ ሁለት ብርጌዶች በመንገድ ላይ፣ በሬጅመንት ቢከፋፈሉ ሊያደርጉ የሚችሉትን ነገር ነው ያሳየው፡፡

በሚያዝያ 8፣ ከጠዋቱ አራት ሰአት ሲሆን፣ ጠቅላይ አዛዡ ከረዳቶቹ ጋር ሆኖ በፈረሰኛ ታጅቦ ወደ ደላንታ አፋፍ ደቡብ አቅጣጫ ሄደ፤ ከዚያም ሆኖ በከፍተኛ ቦታ ላይ ሲሆኑ፣ በደንብ የሚታያውን መቅደላን ለመቃኘት ነበር፡፡ ሪፓርት ሊያደርግም፣ ከመቅደላ ግርጌ የቴዎድሮስ ሠራዊት ድንኳኖችንና ብዙ መድፎችን በምሽጉ ማየቱን ተናገረ፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሊንቀሳቀሱ

---

[114] ከዚህ በፊት በነበረው ትውውቅ፣ ከባላባቶች ጋር ሰላም ለመፍጠር ችሏል፡፡ ስፒዲ፣ ከዚህ ቀደም፣ ለዳውንቱ ባላባት ስለ ለማዳ ዝሆን አጫውቶት ነበር፤ ሆኖም ባላባቱ አላመነውም ነበር፡፡ ስፒዲም ለዘመቻው ከመጡ ዝሆኖች አንዱን አስሬቅዶ ላዩ ላይ በመሳፈር ወደ ባላባቱ በመሄድ የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን በገሃድ አሳይቶ የባላባቱን ስምምነት ማግኘት ችሏል፡፡ ለዚህም ነው የተዘረዘረውን ያህል ቀሰብ ይዞ መምጣት የቻለው፡፡



*የከባድ መሳሪያ ጉዞ መስመር*
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

የታዩ ሲሆን፣ ከካምፑ እሳት የሚነሳው ጭስ ወደላይ እየተጠቀለለ ሲወጣም ይታይ ነበር::

ሰር ሮበርት፣ ቦታውን በጣም ጠንካራ ነው አለ፤ እስካሁን ካየናቸው አምባዎች ሁሉ የበለጠ ነበር፤ ይህ ደግሞ በሁላችንም የነበረውን ሃሳብ አረጋገጠ፤ ማለትም፣ ንጉሡ የበለጠ ጠንካራ ምሽግ ባይኖራቸው ኖሮ በመንገድ ላይ ያየናቸውን ጥሩ አምባዎችን ችላ አይሉም ነበር:: ትልቁ ጥያቄ በሚያረካ መንገድ መልስ አገኘ:: ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ናቸው!

ሰር ሮበርት ከቅኝቱ ሲመለስ፣ ኢንጂነሮቹ መወጣጫ መሰላሎችን መደርመሻዎችን መስራት ጀመሩ፤ ይህም ብዛት ባላቸው ጠንካራ የምሽጉ ገደሎች ለመውጣትና ለማጥቃት ታስቦ ነው::

አእምሯችን ተረጋጋ:: ካምፑም ውስጥ መረጋጋት ሰፍኗል:: ቴዎድሮስ በምሽጋቸው እንዳሉ ታውቋል:: ነገ ከኛ ካምፕ፣ ከደላንታ በደቡብ ጠርዝ ሆነን መቅደላን ማየት አለብን:: ሁሉም የደስታ ስሜት ተሰማው፤ እናም በአቢሲኒያ በእንግሊዝ ካምፕ ውስጥ በደላንታ እንደሆነው እንዲዚህ ሳቅና ጨዋታ ሰምተን አናውቅም::

የሚፎካከሩት የወታደር የሙዚቃ ባንዶች የየራሳቸውን የሚያነቃቁ ሙዚቃዎች ተጫወቱ:: የባህር ሀይል ብርጌዱ የፑንጃቡን ባንድ ጋብዞ ነበር:: የብርጌዱ አባላት በጥንድ መስመር ዙሪያውን ቆርጠው በማለት፣ በመሀከሉ መርከበኞቹ የባንዱን የሚያስደስት ሙዚቃ በመከተል ቀለል ያለ አስደናቂ ውዝዋዜ ያሳዩ ነበር::

ያገሩ ተወላጆች ደግሞ የካምፑን ገበያ ትተው እነዚህ መርከበኞች የሚያሳዩትን ያልተለመደና ሊረዱት ያልቻሉትን እንቅስቃሴ አይኖቻቸውን ከፍተው ነበር የሚያዩት:: ምናልባትም ለአማልክቶቻቸው ፀሎት እያደረጉ ነው ብለው ያመኑት:: ቀስ እያለ ሙዚቃውም አቆመ፤ ሁሉም ወደ ምድብ ቦታው ተመለሰ:: የመጨረሻው ድምፅ ተሰማ፤ መብራቶቹም ጠፉ፤ ነገር ግን በዚህ ብርሃን ባለው የበጋ ሌሊት ማን መተኛት ይችላል?

ከምድሩ ወደላይ ካሉ ከፍሎች ረጋ ያለ ነፋስ እያፏጨ ይመጣ ነበር:: በሰማዩ ላይም የደቡብ መስቀል የሚባለው ኮከብ ከበሽሎ ከልል በላይ ከፍ ብሎ ይታይ ነበር፤ የፐለይዲዝ ከዋከብት ጥርት ብለው ያበራሉ:: ረጭ ያለ ፀጥታ በካምፑ ውስጥ ሰፍኗል፤ የድካም መልእክ ከንዱን የተኙት እንግዶች ላይ ያሳረፈ ይመስል ነበር::